# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
# የተማሪ መጽሐፍ አራተኛ ክፍል



## አራተኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ

# አራተኛ ክፍል

ማዳመጥ መናገር ማንበብ መፃፍ

## ለመፅሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ

የመማሪያ መፅሀፋችሁ የትምህርት ቤቱ ንብረት ቢሆንም እንደራሳችሁ ንብረት መያዝ ይኖርባችኋል፡፡ እንዳይጠፋም ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

1. መፅሀፉን በቀላሉ እንዳይበላሽ በጠንካራ ወረቀት ሸፍኑት
2. መፅሐፉን ደረቅና ቆሻሻ በሌለበት ቦታ አስቀምጡት፡፡
3. መፅሀፉን ለመጠቀም ስትፈልጉ እጃችሁን አፅዱ፡፡
4. በመፅሀፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ በፍፁም አትፃፉ፤ ስዕሎችንም አትሳሉ፡፡
5. ለመፅሀፉ ገፅ መለያ ወይም እልባት ስትፈልጉ ጠንካራ ወረቀት ወይም ክር ተጠቀሙ እንጂ ገፁን አትጠፉ፡፡
6. በመፅሀፍ ውስጥ ያሉትን ገልፆች ወይም ስዕሎች ገንጥላችሁ አታውጡ፡፡
7. የመፅሀፉ ሽፋን ወይም ገፅ ከተገነጠለ በማስትሽ አያይዙ፡፡
8. መፅኀፉ ቦርሳ ውስጥ ሲገባና ሲወጣ እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መፅሀፉን ለሌላ ሰው ስታውሱም ሆነ ስትዋሱ እንዳይቀደድ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
10. መፅሀፉን ስትገልጡት ሽፋንና ገፁ እንዳይገነጣጠል፡፡

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መፅሀፍ


አዘጋጆች:-

ስመኝ ፈጠነ አሰፋ(M.A)

ሪሀና ይሰሐቅ ጀማል (B.A)

አለምነሽ ሮበሌ ፀጋዬ (M.A)

ያለምወርቅ ተስፋዬ (B.A)

አዲስ አዱኛ (B.A)

አስማምቶ አዘጋጆች:-

አለምነሽ ሮበሌ(M.A)

ስመኝ ብረሃኑ (B.A)

የትናየት ማሞ(M.A)

ገምጋሚዎች:-

ለዝና መንግስቴ/B.E.D/

ነፃነት ጥጋቡ/MA/

ይሻሙጌራ ወርቅ/MA/

# መግቢያ

ይህ መፅሀፍ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ መፅሐፉ ለክፍሉ የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ ሲሆን ግቡም የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

በዚህ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ አስር ምዕራፎች አሉ፡፡ በያንዳንዱ ምዕራፍ ወስጥ በየትምርት ይዘቱ ላይ የተመሰረቱ የመናገር ፣የማዳመጥ፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችና ቃላት የሰዋሰው ዕውቀትን ማዳበር የሚያስችሉ ምንባቦች ተመርጠው ተካተዋል፡፡

ምንባቦቹ የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂሎችና የሰዋሰው ዕውቀት ከማዳበር በተጨማሪ አዕምሯቸውን ለማስላት አስተሳሰባቸውን የማበልፀግ ጥቅምም አላቸው፡፡

ምንባቦቹ ከዚህም አልፎ ተማሪዎች ባህላቸውን እንዲረዱና ከሀገራዊ እውነታዎች ጋር እንዲተዋወቁ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ የትምህርቱ አጠቃላይ ግብ ደግሞ ተማሪዎቹ በቀረቡ ይዘቶች አማካኝነት የመናገር፣የማዳመጥ፣የማንበብና የመፃፍ ክሂሎቻቸውን የቃላትና የሰዋሰው ዕውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ማገዝ ነው፡፡

በአጠቃላይ የመማሪያ መፅሀፉ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች እንዲያደብሩ የሰዋሰው ችሎታቸውን እንዲያበለፅጉ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ምንባቦቹ መልመጃዎቹና ተግባራቱ የተማሪዎችን አዕምሮ የማበልፀግ ምናባቸውን የማስፋትና የችግር ፈቺነት አቅማቸውን የማጎልበት ጥቅምም አላቸው፡፡

# የይዘት ማውጫ


ምዕራፍ አንድ................................1
ባህላዊ ልብሶች................................1
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11
ክፍል አራት፡- የሰዋሰው ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 12
የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .13
ምዕራ ሁለት................................14
ቤተሰብ................................14
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 15
ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19
ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 25
ክፍል አራት፡- የሰዋሰው ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26
የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 28
ምዕራፍ ሶስት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
የውሃ አካላት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 30
ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 31
ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 35
የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 38

**ምዕራፍ አራት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 40**

**ተላላፊ በሽታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 40**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 41

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 45

ክፍል ሦስት የቃላት ትምህርት ..............................................47

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 49

**ምዕራፍ አምስት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 50**

**ባህላዊ የሙዚቃ መሰሪያዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 50**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 51

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 54

ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 58

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 59

**ምዕራፍ ስድስት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 60**

**ቦታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 60**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 61

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 63

ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 68

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . 71

**ምዕራፍ ሰባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 72**

**የትራፊክ አደጋ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 72**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 73

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 76

ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 81

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 82

**ምዕራፍ ስምንት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 83**

**ስርዓተ ፆታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 83**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 84

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 86

ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 90

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 91

**ምዕራፍ ዘጠኝ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 92**

**የታዋቂ ሰዎች ታሪክ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 92**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 93

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 96

ክፍል ሶስት፡- ቃላት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 103

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 104

**ምዕራፍ አስር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 105**

**ተረት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 105**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 106

ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 113

ክፍል ሶስት፡- የቃላት ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 118

የክለሳ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 120

# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የተማሪ መማሪያ መፅሀፍ የይዘት ማሳያ

| ገፅ | 1-12 | 13-27 | 28-37 | 38-44 | 45-54 | 55-60 | 61-64 | 65-69 | 70-75 | 76-82 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ | 1 ባህላዊ ልብሶች | 2 ቤተሰብ | 3 የውሃ አካላት | 4 ተላላፊ በሽታዎች | 5 ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ | 6 ቦታዎች | 7 ትራፊክ አደ | 8 ስርዓተ ፆታ | 9 የታዋቂ ሰዎች ታሪክ | 10 ተረት |
| ማዳመጥ | ተነባቢናአናባቢ ድምፆች ንማዳመጥ | የፊደል አጠራር | ትዕዛዞችን አዳምጦ መተግበር | የሚነበበውን ምንባብ ማዳመጥ | የሚነበበውን ምንባብ ማዳመጥ | የሚነበበውን ምንባብ ማዳመጥ | መዝሙሩን ማዳመጥ | ዐረፍተ ነገሮችን ማዳመጥ | ተረቱን ማዳመጥ | ምንባቡን ማዳመጥ |
| መናገር | ውስብስብ ቃላትና ሀረጋትን መናገር | ፊደላትን በማጣመርና በመነጥል መናገር | የድርጊቶች ቅደም ተከል የሰውነት ክፍች | በተለያ አውድ ውስጥ ሰላምታ መለዋወጥ | የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎችን ምስል መናገር | ስዕልን በማየት መናገር ረጅም ተግባቦት መፍጠር | ከ1-10 ያሉትን ቁጥሮች መናገር | ርዕስ መርጦ ንግግር ማቅረብ | ስመናገርራስን መግለፅ ንግግር ማድረግ ታሪክን መናገር | የንግግር መመሪያ ልዩ ልዩ አባባሎች |
| ማንበብ | ምንባብ ማንበብ | ድምፆችን በመለየት ማንበብ | የአባይ ወንዝ | ምንባብ ማንበብ | ምንባብ ማንበብ | አህጉር | ምንባብ ማንበብ | ምንባብ ማንበብ | ጌጤ ዋሚ | ተረት |
| መፃፍ | ስዕሎችን በማየት ስማቸውን መፃፍ | ተራ ዓረፍተ ነገሮችን መፃፍ | ዐረፍተ ነገርን ማሟላት | ለቃላት ተመሳሳይ ፊች መፃፈፍ | ቃላትና ሀረጋትን በባዶ ቦታ አሟልቶ መፃፍ | አንቀጽ መጻፍ | ተመሳሳይ ቃላትን በማዛመድ መፃፍ | ዋና ሀሳብና ማጠቃለያ | ዓረፍተ ነገሮችን በተስማሚ ቃል ማሟላት | ምክንያትና ውጤት |
| ቃላት | ተቃራኒ ቃላትን መፃፍ | ቁሳቁሶችን ከተግባራቸው ጋር ማዛመድ | ቃላትን ማንበብ | ቃላትን በመምረጥ ዓረፍተ ነገርን መሟላት | ስሞችን ከስዕሎች ጋር በማዛመድ መፃፈፍ | ሰላምታ መለዋወጥ | ቃላትን በፊደል ተራ በመደርደር መፃፍ | የቃላት ጨዋታ | የቃላት ተቃራኒ ፍቺ | መደቦችን መለየት አባባሎች |
| ሰዋሰው | አባባሎችን በተሰጠ ው ቃላት ማሟላት | ባህላዊ የመለኪያ መሳሪያዎችን መጠቀም | ዐረፍተ ነገር መመስረት የቃላት አገባብ | | | የዐረፍተ ነገር አወቃቀር | | | ዐረፍተ ነገር ማሟላት | አጭር አንቀፅ |

# ምዕራፍ አንድ
# ባህላዊ ልብሶች

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ሆሄያት ታነባላችሁ
- ውስብስብ ቃል ውስጥ ያሉትን ፊደላት በጭብጨባ እየቆጠራችሁ ትለያላችሁ፡
- ሆሄያቱን በማንበብ ቃላትን ትጽፋላችሁ።
- ውስብስብ ቃላትን ትናገራላችሁ።
- ስዕልን በማየት ስዕሉ ስለምን እንደሚገልፅ በአካል ዕንቅስቃሴ ትገልፃላችሁ
- የባህል ልብሶች ከሌሎች የልብስ አይነቶች የሚለዩበትን ትናገራላችሁ።
- ስዕሎችን በማየት ስማቸውን ትፅፋላችሁ።
- በሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ሆሄያት በመጠቀም ባለ ሁለት ሆሄ ቃላትን ትፅፋላችሁ።
- ለተሰጡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ትፅፋላችሁ።
- የተሰጡትን ቃላት በባዶ ቦታው በመተካት ዓረፍተ ነገሩን ታሟላላችሁ።

# ክፍል አንድ

## 1. ማዳመጥና መናገር

### 1.1 ማዳመጥ

**ተግባር አንድ**

ሀ. የሚከተሉትን ሆሄያት መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ አዳምጣችሁ እንደገና ጥሯቸው፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |

ለ. ውስብስብ ቃላት ውስጥ ያሉትን ፊደላት በጭብጨባ በመታገዝ አዳምጡና መልሳችሁን ተናገሩ፡፡

1. ተንኳኳ
2. ይመኙሻል
3. አሰለፏቸው
4. ክንብንብ

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነብላችሁን ምንባብ ከማዳመጣችሁ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. ሰዎች በአካባቢያችሁ የሚለብሷቸው የልብስ አይነቶችን ተናገሩ፡፡
2. የምታውቋቸውን የልብስ አይነቶች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. የልብስ አስፈላጊነትን ተናሩ፡፡

ለ. ባዳመጣችሁት ምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ለሰው ልጅ መሰረታዊ ነገር ነው ተብሎ የተጠቀሰው የትኛው ነው?

    ሀ. ልብስ ለ. መኪና ሐ. መሬት መ. ደብተር

2. ልብሶች አካላችንን ከምን ይከላከላሉ?

    ሀ. ከብርድ ለ. ከሙቀት ሐ. ከፀሐይ መ. ሁሉም

3. የልብስን መጠን የሚገልፀው ቃል የትኛው ነው?

    ሀ. ጋቢ ለ. አጭር ሐ.ጥቁር መ. ነጭ

4. ልብስ ብርድና ሙቀትን ከመከላከል ውጭ ለምን ይጠቅማል?

    ሀ. ለውበት ለ. ለምግብነት ሐ. ለጊዜ ማሳለፊያ መ.ለሁሉም

5. አካላችንን ከብርድ ለመከላከል መልበስ ያለብን የትኛውን ልብስ ነው?

    ሀ. ስስ ልብስ ለ. ወፍራም ልብስ ሐ.ነጭ ልብስ መ. ውብ ልብስ

## 1.2. መናገር

### 1. ድምፆች

### ተግባር አንድ

**ሀ. የሚከተሉትን ድምፆች በቃል ጥሯቸው**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |

**ለ. ውስብስብ ቃላትና ሐረጋትን በትክክል በማንበብ ተናገሩ።**

1. አስመለሰቻቸው
2. አደነጋገራቸው
3. ስለተሳካላት
4. በትክክል አስቀመጠቻቸው
5. በዝርዝር አስነበበቻቸው

# ክፍል ሁለት

## 2. ማንበብና መፃፍ

### 2.1. ማንበብ

#### ተግባር አንድ


**ሀ. ስዕሉን በማየት በአካል እንቅስቃሴ ግለፁ**



ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ



ረ.

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ለ.ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. በአካባቢያችሁ የሚለበሱ ባህልዊ የልብስ አይነቶችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. ባህላዊ ልብሶች የሚለበሱበትን ጊዜ ተናገሩ፡፡

## የባህል ልብስ

ባህላዊ ልብሶች ከዘመናዊ ልብሶች ተለይተው የሚታወቁባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህም ማለት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚለበሱ መሆናቸው ሲሆን አጋጣሚዎቹም ለበዓላት፣ ለሰርግ፣ ለልደት ለተለያዩ ዝግጅቶች የምንለብሳቸው ናቸው፡፡

ባህላዊ ልብሶች ከዘመናዊ ልብሶች ተለይተው የሚታወቁባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህም ማለት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚለበሱ መሆናቸው ሲሆን አጋጣሚዎቹም ለበዓላት፣ ለሰርግ፣ ለልደት ለተለያዩ ዝግጅቶች የምንለብሳቸው ናቸው፡፡

ባህላዊ ልብሶች የምላቸው በርኖስ፣ ባና፣ ጋቢ፣ ጀለቢያ፣ ቡሉኮ፣ እጀ ጠባብ፣ ጥበብ ቀሚስ የመሳሰሉት እንደመሆናቸው መጠን እነዚህ ልብሶች ቆየት ያሉና የእያንዳንዱን ማህበረሰብ ወግና ባህል የሚያንፀባርቁ ከአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች የሚሰሩ ናቸው፡፡ ምሳሌ ጋቢ በእንዝርት ከተፈተለ ጥጥ የሚሰራ ልብስ ነው፡፡

ሌሎችም ከሀር፣ ከበግ ፀጉር እና ከመሳሰሉት ይሰራሉ፡፡ ባህላዊ ልብሶችን ከልጅ እስከ አዋቂ የሚለብሱት ሲሆን ኢትዮጵያውያንም ከሌሎች ሀገሮች የሚለዩበት አንዱ መገለጫቸው እንደ መሆኑ መጠን እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ ባህሉ ሳይበረዝና ሳይቀየጥ የራሱን ማንነት ማቆየት የሚችልበት መልካም አጋጣሚ ነው ፡፡

ሐ. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማደድረግ ትክክለኛውን ሀሳብ የያዘውን ዐረፍተ ነገር ‹‹ እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ‹‹ሐሰት›› በማለት ፃፉ፡፡

1. ባህላዊ ልብሶች ዘወትር የሚለበሱ ናቸው፡፡
2. ከባህላዊ ልብሶች ውስጥ አንዱ ጋቢ ነው፡፡
3. ባህላዊ ልብሶች በአብዛኛው የሚሰሩት ከጥጥ ብቻ ነው፡፡
4. ባህላዊ ልብሶች እንደ ማህበረሰቡ ባህል ይለበሳሉ፡፡

መ. በምንባብ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ መርጣችሁ ተናገሩ፡፡

1.የባህል ልብስ የሚዘጋጀው ከምንድ ነው?

ሀ. ከጥጥ ለ. ከሐር ሐ. ከበግ ፀጉር መ. ሁሉም

2. የባህል ልብስ የሚለበሰው መቼ ነው?

ሀ. ዘወትር ለ. ለክብረ በዓላት ሐ. ሁል ጊዜ መ.ማታ ማታ

3. ባህላዊ ልብሶችን የሚለብሱት እነማን ናቸው?

ሀ. ሴቶችና ወንዶች ልጆች ብቻ

ለ. ከልጅ እስከ አዋቂ እንደየ ባህላቸው

ሐ. ትላልቅ ሰዎች ብቻ

መ. መልሱ አልተገለፀም

ሠ. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. በብርድ ወቅት የሚለበሱ ልብሶችን ተናገሩ፡፡
2. በስዕሉ ላይ የሚታዩት ልብሶች ምን አይነት ቀለማት አሏቸው?

## 2.2. መፃፍ


### ተግባርአንድ

ቀላል ቃላትን መፃፍ

ስዕሎች



ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ



ረ.

### ሀ. ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በማየት ስማቸውን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ስዕል ሀ. ብርጭቆ

1. ስዕል ለ.--------------------
2. ስዕል ሐ.----------------------
3. ስዕል መ.----------------------
4. ስዕል ሠ.----------------------
5. ስዕል ረ.----------------------

### ለ. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ሆሄያት በመገጣጠም በምሳሌው መሰረት ባለ ሁለት ሆሄ ቃል ፃፉ፡፡፣

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በ | ረ | ሄ | መ | ተ | ጠ |
| ከ | ሳ | ሸ | ላ | ራ | ቀ |
| ኛ | ጣ | ዘ | ወ | ዱ | ሀ |

ምሳሌ፡- በራ ላላ

ሀ.-------------

ለ.-------------

ሐ.-------------

መ.------------

ሠ.-------------

# ክፍል ሶስት

## 3.ቃላት

### ተግባር አንድ

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| ‹‹ ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ወረደ | ሀ. ከሳ |
| 2. ወፈረ | ለ. ትልቅ |
| 3. አጭር | ሐ. ወጣ |
| 4. ትንሽ | መ. ነጭ |
| 5. ጥቁር | ሠ. ረዥም |

## 4. ሰዋሰው

### ተግባር አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በመምረጥ በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይታያሉ | ወጣች | በረረ | ፀሐይ |
| ዘነበ | | | |

1. ፊቷ እንደ ------------------------- ያበራል።
2. አሞራው በሰማይ ላይ ---------------------።
3. በምሽት ጨረቃዋ -------------------------።
4. በሰማይ ላይ ክዋክብቶች ------------------።
5. ዝናቡ በጠዋት ----------------------------።

## የክለሳ ጥያቄ

**ሀ. በተሰጡት ቃላት ዐረፍተ ነገር ስሩ።**

1. ጫወታ
2. ተማረ
3. ጎጂ
4. መጋበዝ
5. ወፈረ
6. ዘፈነ

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ፃፉ።**

1. በላ
2. ጎጂ
3. ደግ
4. ከተማ
5. ታታሪ

# ምዕራፍ ሁለት
# ቤተሰብ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የፊደላትን ድምፅ ለይታችሁ ትጠራላችሁ፡
- ፊደላትን በመነጠልና በማጣመር ትናገራላችሁ፡፡
- ምንባቡን አንብባችሁ ለጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ፡
- ሀረጋትን በትክክል አንብበው ለጓደኞቻቸው ትናገራላችሁ፡፡
- የድርብ ሆሄያትን ድምፅ በመለየትትፅፋላችሁ፡፡
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ ተራኪ ስዕሎችን ታስተካክላላችሁ፡፡
- ተራ ዐ.ነገሮችን ትፅፋላችሁ፡፡
- ባህላዊ የመለኪያ መሳሪያዎችን ለይታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- ባህላዊ የወጥ ቤት ዕቃዎችን ከመስሪያ ቁሳቁሶች ጋር በማዛመድ ትፅፋላችሁ፡፡
- ሶስተኛ መደብ ተውላጠ ስሞችን በመለየት ትናገራላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ

## 1.ማዳመጥና መናገር

### 1.1. ማዳመጥ

#### ተግባር አንድ

የፊደል አጠራር

የሚከተሉትን ፊደላት አንብቧቸው፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |

ሀ. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ሆሄያት መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ አዳምጣችሁ እንደገና ጥሯቸው።

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ሀምስ | ሣድስ | ሣብዕ |
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ሰላምታን መለዋወጥ ለምን ይጠቅማል?
2. ማታ ወደ መኝታችን ስንሄድ ምን ተባብለን እንለያያን?

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት ››ትክክል ካልሆነ ‹‹ሐሰት›› በማለት መልሱ።

1. ጠዋት ስንገናኝ እንደምን ዋላችሁ እንባባላለን።
2. ሰዎች ወደ ሌላ ጉዳያቸው ከመግባታቸው በፊት ሰላምታ መለዋወጥ አለባቸው
3. እንደምን አመሻችሁ የሚለው በቀን የሚሰጥ ሰላምታ ነው።

መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቡድን ተወያያታችሁ ትክክለኛውን መልስ መልሱ።

1. በክፍል ውስጥ ተነስታችሁ እርስ በእርስ ሰላምታ ተለዋወጡ ።
2. ጠዋት ስትገናኙ ምን ተባብላችሁ ሰላምታ ትለዋወጣላችሁ? ተናገሩ።
3. ማታ ስትለያዩ ምን ተባብላችሁ ትለያያላሁችሁ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ
4. አኩለ ቀን የተገናኘ ሰው ምን ተባብሎ ሰላምታ ይለዋወጣል?

## 1.2. መናገር

ፊደላትን ማጣመርና መነጠል

### ተግባር አንድ

ሀ. በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ፊደላት በማጣመር ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ምሳሌ፡- ጠ+ጣ= ጠጣ

ሰ + በ + ረ = ሰበረ

1. ጫ + ማ=------------
2. ከ + ሰ + ል = --------
3. ቡ + ና = ----------

### ለ. በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ፊደላት በመነጣጠል ለመምህራችሁ ተናገሩ፡

ተማረ= ተ + ማ + ረ

ከበደ = ከ + በ + ደ

1. ለበሰ = -----------------
2. ተኛ =------------------
3. ከተማ =---------------

| ማስታወሻ |
|---|
| ሀረግ ማለት ከሁለት ቃላት የተመሰረተ ሆኖ ሙሉ ሀሳብን የሚያስተላልፍ ወይም ያላለቀ ሀሳብ ነው፡፡ |

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ጥቁር ሹራብ | የተቆላ ቡና |
| ከአራት ኪሎ | የአማርኛ መፅሀፍ |
| የሶስተኛ ክፍል | የሰው ቤት |

### ሐ. የሚከተሉትን ሀረጋት በማንበብ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ቡና በወተት | መ. ኳስ ተጫውታ |
| ለ. ቁርሷን በልታ | ሠ. የቤት ስራ ሰርቶ |
| ሐ.ደብተር ይዘው | ረ. ማስክ አድርጋ |

# ክፍል ሁለት

## 2. ማንበብና መፃፍ

### 2.1.ማንበብ

ቤተሰብ

ድምፆችን መለየት

**ተግባር አንድ**

ሀ/ የሚከተሉትን ባለ ድርብ ድምፅ ፊደላት አንብቧቸው፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሏ | ሟ | ሯ | ሷ | ሿ | ቋ | ቧ |
| ቷ | ቿ | ኋ | ኗ | ኟ | ዟ | ዧ |
| ጿ | ጧ | ጯ | ኳ | ጓ | ፏ | |
| ዷ | ጇ | | | | | |

ለ. የድርብ ሆሄያትን ድምፅ በመለየት ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ቃላቱን አንብቡ

ሀ. ተቋማት    ለ. ፏፏቴ    ሐ. ቋንቋ    መ. ልጇ

ሠ. ተንኳኳ    ረ. ተሟሟቀ

**ቤተሰብ**

**ቅድም ምንባብ ጥያቄ**

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. ቤተሰብ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የቤተሰብ አባለት የሚባሉት እነማን ናቸው?
3. በቤተሰብ ውስጥ የልጆች የስራ ድርሻ ምንድነው?

## ቤተሰብ

የአቶ ደምሴ ቤተሰብ አባላት ይዋደዳሉ፡፡ እርስ በርሳቸውም ይከባበራሉ፡፡ ሲፈንና ረቢራ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱት አንድ ላይ ነው፡፡ ረቢራ የሲፈን ታናሽ ወንድም ስለሆነ ትንከባከበዋለች፡፡ አደጋ እንዳያጋጥመው ትጠብቀዋለች፡፡ ረቢራ ለሲፈን ያስብላታል፡፡ ሁለቱም ይተሳሰባሉ፡፡ ረቢራ እና ሲፈን አባትና እናታቸውን ይወዳሉ፡፡ እነሱም ያጋጠማቸውን ችግር ሳይዋሹ ለአባትና ለእናታቸው ይናገራሉ፡የአቶ ደምሴና የወይዘሮ አበባ ቤተሰብ ጥሩ ቤተሰባዊ ስነ-ምግባር ያላቸው ናቸው፡፡ ምክኒያቱም ሁሉም ይዋደዳሉ፤ ይከባበራሉ፤ይተሳሰባሉ፤ ይግባባሉ፤ይተባበራሉ፤ይረዳዳሉ፤ ይተማመናሉ፤ ችግራቸውንም በጋራ ይፈታሉ፡፡ ረቢራና ሲፈን ትምህርታቸውን በንቃትከመማራቸው ባሻገር፤ እናትና አባታቸውን በስራ ያግዛሉ፡፡ የቤተሰብ ኑሮ በመተጋገዝና በመረዳደት ላይ የተመሰረተ ነው፡ ፡ሁሉም የቤተሰበው አባላት ስራውን በአግባቡ ከሰራ ቤተሰብ ደስተኛ ይሆናል፡፡

(ምንጭ፡- መሀመድ አቡበከርና ደመቀ መኩሪያ፡፡(2003) የሳይንስ አጋዥ ገፅ 38-39 ለአራተኛ ክፍል በሚመጥን ተሻሽሎ የተወሰደ ፡፡



ሐ. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማደድረግ ትክክለኛውን ሀሳብ የያዘውን ዐረፍተ ነገር ‹‹ እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ‹‹ሐሰት›› በማለት ፃፉ፡፡

1. የቤተሰብ አባላት ማለት የክፍል ጓደኛንም ያጠቃልላል፡፡
2. መዋደድ፤መከባበርና መተሳሰብ የመልካም ስነምግባር መገለጫ ነው፡፡
3. በምበባቡ ውስጥ የተጠቀሱት የቤተሰብ አባላት ችግራቸውን በጋራ ይፈታሉ
4. የቤተሰብ አባላት ስራውን በአግባቡ ከሰራ ቤተሰብ ደስተኛ ይሆናል፡፡

መ. በምንባቡ መሰርት በምድብ ‹‹ሀ›› ስር ለተዘረዘሩ ቃላቶች በ‹‹ለ›› ስር ካሉት ጋር ተስማሚያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| ‹‹ ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ስራ | ሀ. መጥፎ ስነ ምግባር |
| 2. ቤተሰብ | ለ. በቤት ውስጥ አብረው የሚኖሩ ሰዎች |
| 3. መማር | ሐ. የልጆች የስራ ድርሻ |
| 4. መሳደብ | መ. ተግባር |

ሠ. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ረቢራ የሲፈን ታናሽ ወንድም ስለሆነ ---------------።

ሀ. ትጠብቀዋለች ለ. ትንከባከበዋለች ሐ. ይተሳሰባሉ መ. ሁሉም

2. ልጆቹ ያጋጠማቸውን ችግር ለቤተሰብ --------------------።

ሀ.ይደብቃሉ ለ. ይናገራሉ ሐ. ያነባሉ መ.ሁሉም

3. የቤተሰብ ኑሮ በመተጋገዝና-----------ላይ የተመሰረተ ነው።

ሀ. በመዝናናት ለ. በውይይት ሐ. በመረዳዳት መ. በክርክር

## 2.2. መፃፍ

### ተግባር አንድ

ሀ. ተዘበራርቀው የተቀመጡት ተራኪ ስዕሎችን በቡድን በመወያየት ቅደም ተከተላቸውን አስተካክላችሁ ፃፉ።



ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ.




ረ.

ማስታወሻ

ተራ ዐነገርን መፃፍ

ዓረፍተ ነገር ማለት ሙሉ ሀሳብን ማስተላለፍ የሚችል ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

እግሯን ታጠበች፡፡

የቤት ስራ ሰራ፡፡

ለ. በክብ ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ገዛ　　በላ　　ሸጠ

ምግብ

አስቀመጠ　　ሰራ　　ሰጠ

ምሳሌ ፡-ምግብ በላ፡፡

1. ምግብ ------------፡፡

2. ምግብ ------------፡፡

3. ምግብ------------፡፡

4. ምግብ-------------፡፡

5. ምግብ------------፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3. ቃላት

### ባህላዊ የወጥ ቤት ዕቃዎች



ሳህን



ጮጮ



ከቀንድ የሚሰራ የውሃ መጠጫ



ጣባ



የእንጨት ማማሰያ



የሸክላ ድስት



የሸክላ ምጣድ



ጭልፋ



የቀንድ ማንኪያ

# ክፍል አራት

## 4.ሰዋሰው

### ተግባር አንድ

**ሀ. በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዐ.ነገር ስሩ፡፡**

ምሳሌ፡- ቡና በጀበና ይፈላል፡፡

የከድር ጫማ ማሰሪያ ተበጠሰ፡፡

ሀ. እንስራ

ለ. የቀንድ ማንኪያ

ሐ. መሶብ

ሠ. ሰፌድ

መ. ጮጮ

**ለ. በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን የሚሰሩ ነገሮች በ‹‹ለ››ስር ካሉት የመስሪያ ቁሳቁሶች ጋር አዛምዱ፡፡**

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. የወጥ | ሀ. መሶብ |
| 2. የእንጀራ | ለ. ቤት |
| 3. የጀበና | ሐ. ድስት |
| 4. የሸክላ | መ. ቡና |
| 5. የቀንድ | ሠ. ማንኪያ |

ማስታወሻ

ባህላዊ የመለኪያ መሳሪያዎች

ባህላዊ መለኪያ መሳሪያዎች የሚባሉት ፡-እርምጃ ፣ስንዝር ፣ክንድ ፣ ጣሳ፣ ስልቻ፣ ቁና፣ እንቅብ ፣ገመድ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ተግባር አንድ

ሀ. በዶ ቦታዎቹን በተስማሚው ቃል አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| እርምጃ | ስንዝር | ክንድ | ጣሳ |
| እሱ | እሷ | እነሱ | |

ምሳሌ፡-

እሱ <u>በስንዝር</u> ልብሱን ለካ፡፡

እሷ <u>በእርምጃ</u> መሬቱን ለካች፡፡

እነሱ <u>በገመድ</u> መሬቱን ለኩ፡፡

1. እህሉን በ ------------ ሰፈረ፡፡
2. ረሂማ ጨርቁን በ-------------- ለካች፡፡
3. ------------ቤቱን በእርምጃ ለኩ፡፡
4. ተማም በ-----------መሬቱን ለካ፡፡
5. ----------- ቡናውን በስኒ ሰፈረች፡፡

## የክለሳ ጥያቄ

**ሀ. ለሚከተሉትን ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን በመፈለግ አዛምድ።**

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. መተጋገዝ | ሀ. ተከታታይ |
| 2. ይግባባሉ | ለ. መረዳዳት |
| 3. ጥሩ | ሐ. ይስማማሉ |
| 4. ታናሽ | መ. መልካም |

**ለ. የሚከተሉትን ሆሄያት በማጣመር ቃላት መስርቱ።**

1. አ + ለ + ቀ + ሰ =-----------
2. ተ + ማ + ረ=--------------
3. ቀ + ሰ + መ=------------

**ሐ. የሚከተሉትን ቃላት በመነጠል ፃፉ።**

1. ተመለሰ=-------------
2. መታ=----------------
3. ወደቀ=--------------

# ምዕራፍ ሶስት
# የውሃ አካላት

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ**

- ስለውሃ አካላት ያዳመጣችሁትን ትናገራላችሁ፡፡
- የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ትናገራላችሁ፡፡
- የሰውነት ክፍሎችን ትናገራላችሁ፡፡
- የቃላት ጥምረት ግንዛቤያችሁን ታሰፋላችሁ፡፡ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤትና የቤት ውስጥ እንቅስቃሴን የሚገልጹ ቃላትን ትፅፋላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ

## ተግባር አንድ፡-ማዳመጥ

ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ "የውሃ አካላት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ፡፡ከዚያም ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የውሃ አካላት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከውሃ አካላት መካከል ሶስቱን ጥቀሱ፡፡
3. ከውሃ አካላት ሰፊውን ክፍል የያዘው የቱ ነው?

## ተግባር ሁለት፡-መናገር

ሀ. መምህራችሁ ስለየውሃ አካላት የሚያነቡላችሁን ምንባብ በጥሞና በማዳመጥ የምንባቡን መልዕክት ተናገሩ፡፡

ለ. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የምግብ አይነቶች አንዱን በመምረጥ እንዴት እንደሚዘጋጁ በቅደም ተከተል ፅፋችሁ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡

1. ቡነ ቀላ
2. ጩምቦ
3. ጨጨብሳ
4. ገንፎ

ሐ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት የሰውነት ክፍሎችን አንድ በአንድ እየተነሳችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

ሀ. ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የወንዞች ስም ተናገሩ፡፡
2. ወንዞች ምን ምን ጥቅም እንዳላቸው ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. ስለአባይ ወንዝ ከአሁን በፊት የሰማችሁት ነገር አለ? ካለ ለመምህራቸው ተናገሩ፡፡

## የአባይ ወንዝ

በዓለማችን ላይ ካሉ ወንዞች መካከል አንዱ የአባይ ወንዝ ነው፡፡የአባይ ወንዝ በርዝመቱ ከዓለም አንደኛ ነው፡፡የአባይ ወንዝ መነሻ ኢትዮጵያ ነው፡፡ከጎጃም ሰከላ ከሚባል አካባቢ በመመንጨት በጣና ላይ አርፎ የሚያልፍ ትልቁ የውሃ ሀብታችን ነው፡፡ወደ አባይ ወንዝ የሚፈሱ ሌሎች ገባር ወንዞችም አሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ዲዴሳ፣ዳቡስ፣ጉደር፣አንገር፣ሙገር፣ፊንጫአ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ወንዛችን ከአገራችን አልፎ ወደ ሌሎች አጎራባች ሀገሮች የሚፈስ ነው፡፡

አባይ ከኢትዮጵያ ሲነሳ ጥቁር አባይ በመባል የሚጠራ ሲሆን ካርቱም ሱዳን ሲደርስ ከነጭ አባይ ጋር ተገናኝቶ በግብፅ በኩል ወደ ሜዲትራንያን ባህር ይፈሳል፡፡ አባይ በአሁን ጊዜ በመገደብ ላይ ይገኛል፡፡



የአባይ ግድብ

## ተግባር አንድ፡-ማንበብ

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. የአባይ ወንዝ መነሻው ኢትዮጵያ ነው።
2. የአባይ ወንዝ ወደ ሌሎች አጎራባች አገሮች የመፍሰስ አቅም የለውም።
3. የአባይ ወንዝ በርዝመት ከዓለም አንደኛ ነው።
4. ወደ አባይ ወንዝ የሚፈሱ በርካታ ወንዞች አሉ።
5. የአባይ ወንዝ ባለቤት ኢትዮጵያ ናት።

## ተግባር ሁለት፡- መፃፍ

### ሀ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. የአባይ ወንዝ በርዝመቱ ከዓለም ስንተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል?

   ሀ. አንደኛ ለ. ሁለተኛ ሐ. ሶስተኛ መ. አራተኛ

2. የአባይ ወንዝ መነሻው የት ነው?

   ሀ. ግብፅ ለ. ሱዳን ሐ. ኢትዮጵያ መ. አይታወቅም

3. የአባይ ወንዝ ተፋሰስ የሆነው የትኛው ወንዝ ነው?

   ሀ. ጊቤ ለ. ዳቡስ ሐ. ዲዴሳ መ. ሁሉም

4. የአባይ ወንዝ ተፋሰስ አገሮች እነማን ናቸው?

   ሀ. ኢትዮጵያ ለ. ግብፅ ሐ. ሱዳን መ. ሁሉም

## ለ. ከዚህ በታች ከምንባቡ የወጡ ቃላትን ፅፋችሁ አንብቧቸው።

1. አባይ
2. ዳቡስ
3. ኢትዮጵያ
4. ጎጃም
5. ርዝመት
6. አለም
7. ሀብታችን
8. ገባር
9. ሜደርትራንያን
10. ካርቱም

## ሐ. በሚከተሉት ከምንባቡ በወጡ ቃላት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

ምሳሌ፡- ኢትዮጵያ፡- የአባይ ወንዝ መነሻው ኢትዮጵያ ነው።

1. ወንዝ
2. አባይ
3. ርዝመት
4. ገባር
5. ሀብታችን
6. ባለቤት

**ማስታወሻ ጥምር ቃላት**

ጥምር ቃላት የሚባሉት ሁለት የተለያየ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በማጣመር አንድ ሌላ ትርጉም የሚሰጥ ቃል ለመፍጠር የሚያስችል ክፍል ነው።እነዚህ የተጣመሩት ቃላት በፊት ለየብቻ የነበራቸውን ትርጉም ሙሉ በሙሉ በመልቀቅ ተጣምረው ሌላ ትርጉም በመስጠት ይታወቃሉ።

ለምሳሌ፡- ቤት + መፅሐፍ = ቤተ-መፅሐፍት

አየር + ወለድ = አየር-ወለድ

# ክፍል ሶስት፡-ቃላት

## ተግባር አንድ፡-ቃላት

ሀ. ከዚህ በታች ጥምር ቃል ለመመስረት የሚያስችሉ ቃላት ቀርበዋል፤ ቃላቱን በማገናኘት ጥምር ቃላትን መስርቱ፡፡

1. ሰው + ሰራሽ = ______________________
2. አይን + አፋር = ______________________
3. ልብ + ወለድ = ______________________
4. ወዝ + አደር = ______________________
5. ውሃ + ወለድ = ______________________
6. ህብረት + ሰብ = ______________________
7. ልብ + ቢስ = ______________________
8. አይን + ስውር = ______________________
9. ቁም + ሳጥን = ______________________
10. ህይወት + አድን = ______________________

ሐ. የቃላትን የአሰላለፍ ቦታ በመለዋወጥ የትርጉም ለውጥ ማምጣታቸውን በፅሁፍ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ጠሳ= ሳጠ

ሰረቀ = ቀሰረ

1. ሳቀ
2. ሳመ
3. ለማዳ
4. ቀሰቀሰ
5. በሳ

መ. ከዚህ በታች ያሉትን ቃላት በመጠቀም ባዶ ቦታውን አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀብት | ጥንታዊ | ባህል |
| ማህበራዊ | ዘመን | ጠንክሮ |

1. ------------ መስተጋብር መፍጠር ተገቢ ነው፡፡
2. ------------ ቅርሶቻችንን መንከባከብ አለብን፡፡
3. የአባይ ወንዝ የኢትዮጵያ ------------ነው፡፡
4. ውጤታማ ለመሆን ----------- መስራት ያስፈልጋል፡፡
5. የኦሮሞ ----------- የራሱ የሆነ መገለጫ አለው፡፡

ማስታወሻ ፡-፡

ተውላጠ ስም ማለት በስም ምትክ በተለዋጭነት የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡ ለምሳሌ /ቶላ/ ለማለት/ እሱ/ ፧/ዝናሽ/ ለማለት /እሷ/ብዙ ሰዎች ሲሆኑ /እነሱ /እያልን የምንጠራው ነው፡፡

ምሳሌ ፡- -ደቻሳ ቁርሱን በላ፡፡

እሱ ቁርሱን በላ፡፡

- ዱሬቲ የቤትስራ ሰራች፡፡

እሷ የቤትስራ ሰራች፡፡

4. ሰዋሰው

## ተግባር አንድ

ሀ. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ

1. አብዱ ከትምህርት ቤት መጣ። አብዱን ተክቶ የሚገባው ተውላጠ ስም-----ነው

ሀ. እነሱ ለ. እሷ ሐ.እሱ መ.ሁሉም

2. ሀሊማ ምሳዋን በላች። ሀሊማን ተክቶ የሚገባው ተውላጠ ስም------ነው።

ሀ. እሷ ለ.እነሱ ሐ.አንቺ መ. እኔ

3. ብርሃኑ፣ጀማል እና ማርታ ወደቤታቸው ሄዱ። ብርሃኑ፣ ጀማል እና ማርታን ተክቶ የሚገባው ተውላጠ ስም--------------ነው።

ሀ. እሱ ለ. እነሱ ሐ. እሱ መ.ሁሉም

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የውሃ አካላት የሚባሉትን ጥቀሱ፡፡
2. ከሚከተሉት የምግብ አሰራር ሂደቶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ለመምህራችሁ የአሰራሩን ቅደም ተከተል ተናገሩ፡፡

   ሀ. የዶሮ ወጥ አሰራር

   ለ. የጨኮ አሰራር

   ሐ. የእንጀራ አገጋገር

   መ. የጨጨብሳ አሰራር
3. በክፍል ውስጥ ተራ በተራ ፊት ለፊት በመውጣት ከአንገት በላይ ያሉትን የሰውነት ክፍሎች ተናገሩ፡፡
4. ሶስት ጥምር ቃላትን በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
5. ከዚህ በታች የተሰጡትን ዐረፍተ ነገሮች በማየት ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ትርጉም ጻፉ፡፡

   1. በቀለ ምሳ <u>በላ</u>፡፡

      በቀለ ነገር <u>በላ</u>፡፡
   2. አስቴር ቢላዋ <u>ሳለች</u>፡፡

      አስቴር ጉንፋን ስለያዛት ደጋግማ <u>ሳለች</u>፡፡
   3. ከድር ሽንብራዉን <u>ጠረጠረ</u>፡፡

      ከድር ጓደኛውን <u>ጠረጠረ</u>፡፡

4. ፈጠነ መጽሀፉን ወሰደው።

   ፈጠነን ውሃ ወሰደው።

5. አያንቱ በትምህርቷ ወደቀች።

   አያንቱ አዳልጧት ወደቀች።

# ምዕራፍ አራት
# ተላላፊ በሽታዎች

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ስለ ኤች አይቪ ኤድስ በሽታ ትናገራላችሁ፤
- በተለያየ አውድ ውስጥ ንግግር ታደርጋላችሁ፤
- የሰላምታ ልውውጥ ታደርጋላችሁ፤
- ስለ ኤች አይቪ ኤድስ በሽታ አደገኝነት ትወያያላችሁ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ በመስጠት ትፅፋላችሁ፤
- ስለኮሮና በሽታ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ በፅሁፍ ታቀርባላችሁ፤

# ክፍል አንድ

## 1. ማዳመጥና መናገር

### 1.1. ማዳመጥ

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

**ተግባር አንድ**

ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ‹‹ኤች አይቪ ኤድስ›› በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ፅሁፍ ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ኤች አይ ቪ /ኤድስ/ምንድነው?
2. ኤች አይ ቪ /ኤድስ/እንዴት ይተላለፋል?

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆነ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም ለኤች አይ ቪ አድስ በሽታ ያጋልጣል፡፡
2. ኤች አይ ቪ ኤድስ ለሞት የሚያደርስ በሽታ ነው፡፡
3. ኤች አይ ቪ ኤድስ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም አያዳክምም፡፡
4. ህፃናትን ያለ ወላጅ ከሚያስቀሩት በሽታዎች አንዱ ኤች አይ ቪ ኤድስ ነው

## 1.2. መናገር

ሰላምታ የሚለዋወጡ ኡስማንና እናቱ




ኡስማን - እንደምን አደርሽ እማዬ?

እናት - እንደምን አደርክ ልጄ?

ኡስማን - ምን እያደረግሽ ነው?

እናት - ቤት እያፀዳሁ ነው።







**ለ.ቀን የሚያሳይ አረንጓዴ መስክ**

**ቶላ - እንደምን ዋላችሁ? (ማየት የተሳነው ሰው)**

**ጀማል - ደህና እንደምን ዋልክ (በዊልቸር ላይ የጠቀመጠ ሰው)**

**ቶላ - ከስራ ወጥቼ ምሳ ልበላ ነው ና እንብላ?**






## ተግባር አንድ

ሀ. በምስሉ ላይ የቀረበውን የሰላምታ አሰጣጥ በማየት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር የታመመን ሰው መጠየቅ ላይ ያላችሁ በማስመሰል ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡

ለ. ወደ ፊት ለሀገራችሁ በምን ሙያ ላይ ተሰማርታችሁ ሀገራችሁን ማገልገል ትፈልጋላችሁ?

ሐ. ስለ ኤች አይቪ ኤድስ በሽታ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2.ማንበብ መፃፍ

### 2.1 ማንበብ

ተላላፊ በሽታዎች

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

**ተግባር አንድ**

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. ሰዎች በጉንፋን በሽታ መያዛቸውን ልናውቅ የምንችለው እንዴት ነው?
2. ተላላፊ በሽታዎች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

## ተላላፊ በሽታዎች

ተላላፊ በሽታዎች ከህመምተኛ ወደ ጤነኞች በተለያዩ መንገዶች የሚተላለፉ የበሽታ አይነቶች ናቸው፡፡ ተላላፊ በሽታዎች ከሚባሉት መካከል ኤች አይ ቪ ኤድስ ጉንፋን፣ ኮረና፣ የሳንባ ነቀርሳ እና የተቅማጥ በሽታዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የተላላፊ በሽታዎች መነስኤ ቫይረስ፣ ባክቴሪያና ትላ ትል ናቸው፡፡

ተቅማጥ በባክቴሪያ አማካይነት በተበከለ ምግብና ውሃ ይከሰታል፡፡ የተቅማጥ በሽታ በተለይ ህጻናትን ያጠቃል፡፡ በሽታው በንፅህና ጉድለት ምክንያት የሚመጣ ሲሆን በንክኪም ሊተላለፍ ይችላል፡፡

የጉንፋን በሽታ በንክኪ ወይም በትንፋሽ የሚተላለፍ ቫይረስ ነው። የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በአብዛኛው ሳንባን የሚያጠቃ በሽታ ነው፤ሆኖም መተላለፊያ መንገዱ በአብዛኛው በትንፋሽ ነው።

ኮረና በንክኪና በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ ነው። በአጠቃላይ የአካባቢያችንን ንፅህና እና የግል ንፅህናን በመጠበቅ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል።

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ተላላፊ በሽታ የሚባለው ምንድ ነው?

ሀ. በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ

ለ. ሰዎችን የሚጎዳ በሽታ

ሐ. ሰዎችን ለሞት የሚዳርግ በሽታ     መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት መካከል ተላላፊ በሽታ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ጉንፋን     ለ. ኤች አይ ቪ ኤድስ     ሐ. ኮረና

መ. የደም ግፊት

3. ተላላፊ በሽታን እንዴት መከላከል እንችላለን?

ሀ. የግል ንፅህናን በመጠበቅ     ለ. የአካባቢን ንፅህናን በመጠበቅ

ሐ. እጃችንን በሳሙና ቶሎተሎ በመታጠብ     መ. ሁሉም

4. ኮሮና ከሰው ወደ ሰው የማይተላለፍበት መንገድ ?

ሀ. በትንፋሽ     ለ. በጭስ     ሐ. በንፅህና ጉድለት     መ. በንኪኪ

## 2.2. መፃፍ

### ተግባር አንድ

ሀ. ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን በመፈለግ በአዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ተላላፊ በሽታ | ሀ. ማነስ |
| 2. ጥቂት | ለ. ተዛማች |
| 3. የተከበከለ | ሐ. ንፁህ ያልሆነ |
| 4. ጉድለት | መ. ይፈጠራል |
| 5. ይከሰታል | ሠ. አናሳ |

ለ. ሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በቡድን በመወያየት በፅሁፍ መልሱ

1. የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚያጠቃው የትኛውን የአካል ክፍል ነው
2. በኮሮና እንዳንያዝ ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ ምንድነው?

ሐ. ከታች የተሰጡትን ቃላት በመምረጥ ባዶ ቦታ ላይ በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡

| ዝናቡ | ፀሐይ | ብረሃን |
|---|---|---|

1. የዛሬዋ ------------ በጣም ታቃጥላለች፡፡
2. የጨረቃዋ ---------------- ያምራል፡፡
3. በጠዋት-------------- እያካፋ ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄ

### ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን አዛምዱ።

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ወጣ | ሀ. ተንቀዠቀዠ |
| 2. ረጋአለ | ለ. ደካማ |
| 3. ደፈረሰ | ሐ. ሰነፍ |
| 4. ጠንካራ | መ. ገባ |
| 5. ጎበዝ | ሠ. ጠራ |

### ለ. ባዶ ቦታውን በተስማሚው ቃል ሙሉ።

1. እንደምን አደራችሁ የሚለው ሰላምታ በ-------ጊዜ የሚሰጥ ሰላምታ ነው።

2. እንደምን ------------------ የሚለው ሰላምታ በምሽት የሚሰጥ ሰላምታ ነው፡

# ምዕራፍ አምስት
# ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ዋሽንት ከምን እንደሚሰራ በቃል ትናገራላችሁ ፡፡
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ስዕል በመመልከት ስማቸውን አንድ በአንድ ትናገራላችሁ፡
- ስዕሎችን በማየት በቅደም ተከተል ታደራጃላችሁ፡፡
- የምባቡን ፍሬ ሀሳብ ተረድታችሁ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቃላትን በተሰጠው ክፍት ቦታላይ በማስገባት የተሟላ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- አባባሎችን እንደ አገባባቸው ትፅፋላችሁ፡፡
- ቃላትን ከስዕሎች ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- በተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ስርዓታቸውን ጠብቃችሁ ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. ማዳመጥና መናገር

### 1.1. ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ተግባር አንድ**

ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት እነማን ናቸው?
2. ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ ከበሮ ለምን ያገለግላል?

ለ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያቡላችሁን ምንባብ በፅሞና አዳምጣችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. ዋሽንት ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል?
2. ዋሽንት ስንት ቀዳዳዎች አሉት?
3. ዋሽንት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የተባለው ለምንድነው?

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆነ ‹‹ሐሰት›› በማለት በቃል መልሱ።

1. ዋሽንት አስራ ሁለት ቀዳዳዎች አሉት።
2. ዋሽንት ከሸንቦቆ ይሰራል።
3. ዋሽንት ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ይመደባል።

## 1.2. መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥቄዎች በበድን ተወያይታችሁ አጭር መልስ ስጡ።

1. ምስሎቹን በመመልከት ስማቸውን ተናገሩ።
2. መምህራችሁ የሚያሰሚችሁን የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፅ በሚገባ ካዳመጣችሁ በኋላ የምን ድምፅ እንደሆኑ ለይታችሁ ተናገሩ።
3. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን ሊሰሩ እንደሚችሉ በቡድናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።



ከበሮ



ጡሩምባ



ዋሽንት



መስንቆ



ክራር

ለ. የሚከተሉት ስዕሎች በመመልከት በቅደም ተከተላቸው አደራጅታችሁ ተናገሩ።



ሀ.



መ.



ለ.



ሠ.



ሐ.



ረ.

# ክፍል ሁለት

## 2. ማበብና መፃፍ

### 2.1. ማንበብ

**ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች**

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

**ተግባር አንድ**

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ።

1. በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ምን ምን አይነት የሙዚቃ መሳሪያዎች አሉ?
2. የምታውቋቸውን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ተብለው በሁለት ይመደባሉ። ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ቆየት ያለና ከህብረተሰቡ የቆየ ባህል ጋር ተያይዞ የኖረ ነው። እነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ክራር፣ ዋሽንት፣ ከበሮ፣ ማስንቆ፣ ጡሩንባ የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ እነዚህ መሳሪያዎች በአካባቢ ከሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች ይዘጋጃሉ። ክራር ከእንጨትና ከቆዳ ከቀጭን ገመድ ሲሰራ ከበሮ ከእንጨትና ከቆዳ፤ ማስንቆ ከእንጨት ከቆዳና ከፈረስ ጭራ ይሰራል።

ዋሽንት ሸንበቆ ጎኑ ላይ የተለያዩ ቀዳዳዎች ተበጅተውለት ሲዘጋጅ፤ጡሩምባ ደግሞ በአንድ በኩል ጠባብ ቀዳዳ በሌላ በኩል ደግሞ ሰፋ ያለ ቀዳዳ እንዲኖረው ተደርጎ ከቀንድ ወይም ከብረት ሊሰራ ይችላል፡፡ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለተለያየ አገልግሎት ይውላሉ፡፡ ለመዝናኛ፣ ፈጣሪን ለማመስገን፣ሰዎችን ለማድነቅ፣ ብሶትና ደስታን ለመግለፅ፣ ለገቢ ማግኛና ለመሳሰሉት ያገለግላሉ፡፡

## ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው?
2. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን ይሰራሉ?
3. ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ከበሮ ከምን ይሰራል?

## ሐ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚዘጋጁት ከምንድነው?

ሀ. ከቆዳ — ለ. ከፈረስ ጭራ

ሐ. ከእንጨት — መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለምን አገልግሎት ይውላሉ?

ሀ. ለመዝናኛነት — ለ. ፈጣሪን ለማመስገን

ሐ. ለሀዘንና ደስታን ለመገለፅ — መ. ሁሉም

3. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ---------- ነው፡፡

ሀ. ጊታር ለ. ሳክስፎን

ሐ. ክራር መ. ፒያኖ

4. በሰርግና በሀይማኖት በአላት አካባበር ላይ-------------መጠቀም የተለመደ ነው፡፡

ሀ. መስንቆ ለ. ከበሮ

ሐ. ጊታር መ. ሳክስፎን

5. መስንቆ ከምን ከምን ይሰራል?

ሀ. ከእንጨት ለ. ከቆዳ

ሐ. ከፈረስ ጭራ መ.ሁሉም

## 2.2.መፃፍ

### ተግባር አንድ

**ሀ. ከሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት መካከል ትክለኛውን በመምረጥ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ አሟሉ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውበት | ጨለማ | ብርጭቆ | የሙዚቃ መሳርያ | መጫወት |

1. የአካባቢው -----------------በጣም ደስ ያሰኛል፡፡
2. ቤቱ መብራት ስለሌለው --------------ነው፡፡
3. ጫልቱ ------------------- ሰበረች፡፡
4. ልጁ ------------------መጫወት ይወዳል፡፡
5. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ -----------ደስ ይላል፡፡

**ለ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በምሳሌው መሰረት አሟሉ፡፡**

ምሳሌ፡- ዋሽንት ይነፋል ካልን

ሀ. ከበሮ------------------------------፡፡

ለ. መሰንቆ ----------------------------፡፡

ሐ. ጡሩንባ------------------------- ፡፡

**ሐ.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. በዋሽንት እየታጀበ የሚዘፈን የኦሮምኛ ዘፈን ታውቃላችሁ? ዘፈኑን እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ፡፡
2. ስለ አንድ የምታውቁት የሙዚቃ መሳሪያ ግጥም ፅፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3.ቃላት

### ተግባር አንድ

ሀ. በ‹‹ሀ››ረድፍ የተሰጡትን ስሞች በ‹‹ለ››ረድፍ ከተሰጡት ምስሎች ጋር በማዛመድ ፃፉ::

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› | |
|---|---|---|
| 1. ከበሮ | ሀ |  |
| 2. ዋሽንት | ለ |  |
| 3. መሰንቆ | ሐ |  |
| 4. ጡሩምባ | መ |  |

ለ. በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዐረፍተ ነገር ስሩባቸው።

ምሳሌ፡- ልጁ በታክሲ ወደ ቤቱ ሄደ።

1. ታክሲ
2. ቤት
3. ችግኝ
4. መፅሀፍ
5. ዩኒፎርም
6. ጆለቢያ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

   1. ሙዚቃ ምንድን ነው?
   2. የሙዚቃ መሳሪያዎች በስንት ይከፈላሉ? ስማቸውን ጥቀሱ?
   3. የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ከምን ሊሰሩ ይችላሉ?

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ጻፉ።

   1. ትልቅ-----------------
   2. አጭር-----------------
   3. ሄደ------------------
   4. ክፉ-------------------
   5. ቆንጆ-----------------

# ምዕራፍ ስድስት
# ቦታዎች

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለቦታዎች ምንነት ያዳመጣችሁትን ትናገራላችሁ፡፡
- በስልክ ሰላምታን ትለዋወጣላችሁ፡፡
- ረጃጅም ተግባቦትን በክፍል ውስጥ ትለዋወጣላችሁ፡፡
- የቃላት ግንዛቤያችሁን ለማሳደግ የምታደርጉትን ጥረት ታሳያላችሁ፡፡
- የደስታ መግለጫ አገላለጾችን ትፅፋላችሁ፡፡
- የዐረፍተ ነገር አወቃቀር መመሪያን በመከተል የተስተካከለ ዐረፍተ ነገር ትፅፋላችሁ፡፡
- ዐረፍተ ነገሮችን በማገናኘት ወደ አንቀጽ ቀይራችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ሐሳባችሁን ትገልጻላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥና መናገር

## ተግባር አንድ፡- ማዳመጥ


ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ "ቦታዎች" የተሰኘ ምንባብ ላይ የቀረበውን ሐሳብ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ፡፡ በመቀጠል ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. ቦታዎች ማለት ምን ማለት ነው?
2. ታሪካዊ ቦታዎች የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
3. በሀገራችን ታዋቂ ከሆኑ ታሪካዊ ቦታዎች ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ፡፡

## ተግባር ሁለት፡-መናገር

ሀ. መምህራችሁ ስለቦታዎች ያነበቡላችሁን ምንባብ በጥሞና በማዳመጥ በምንባቡ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ ደግማችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. የሚከተሉትን ስዕሎች ተመልክታችሁ የምን ምን ቦታዎች እንደሆኑ ለመምህራችሁ ንገሯቸው።





















ሐ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በስልክ ሰላምታ እንዴት እንደምትለዋወጡ በተግባር አሳዩ፡፡

መ. የደስታ መግለጫ አገላለጾችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ ተነጋገሩ፡፡

ሠ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ረጃጅም ተግባቦትን ተጠቅማችሁ ሃሳብ ተለዋወጡ፡፡

ለምሳሌ፡- ሀ. ስለ ህዳሴ ግድብ

ለ. ስለ ሶፍኡመር ዋሻ

ሐ. ስለአባጅፋር ቤተ መንግስት

## ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መጻፍ

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**


ሀ. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ ፡፡

1. ስለ አህጉር የምታዉቁትን ተናገሩ፡፡
2. በዓለም ላይ ስንት አህጉራት ይገኛሉ?
3. ሀገራችን ኢትዮጵያ በየትኛው አህጉር ውስጥ ትገኛለች?

## አህጉር

አህጉር ማለት በውቂያኖስ የተለዩ የሰፋፊ መሬቶች መጠሪያ ነው። በአለማችን ላይ ሰባት አህጉራት አሉ።

እነሱም፡-እስያ፣አፍሪካ፣ሰሜን አሜሪካ፣ደቡብ አሜሪካ፣አንታርቲካ፣አውሮፓና አውስትራሊያ ናቸው። እነዚህ የተዘረዘሩት አህጉራት በቅደም ተከተል ከአንድ እስከ ሰባት(1-7) የተቀመጡት በቆዳ ስፋት ከትልቅ እስከ ትንሽ የተዘረዘሩ ናቸው።



የአለም ካርታ

**ተግባር አንድ፡- ማንበብ**

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. በአለም ላይ ያሉ አህጉራትን ዘርዝሩ፡፡
2. በቆዳ ስፋቷ ቀዳሚ የሆነች አህጉር ማን ናት?
3. በቆዳ ስፋቷ ዝቅተኛ የሆነች አህጉር ማን ናት?
4. በቆዳ ስፋቷ ሁለተኛ የሆነችው ማነች?እናንተ የምትገኙት በየትኛው አህጉር ውስጥ ነው?

**ለ. ከላይ ከምንባቡ ጋር የቀረበውን ካርታ በመመልከት አህጉራቱ የሚገኙበትን አቅጣጫ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. በአለም ላይ አምስት አህጉራት ብቻ ይገኛሉ፡፡
2. በውቅያኖሶች የተከበቡ ሰፋፊ ቦታዎች አህጉራት ይባላሉ፡፡
3. በቆዳ ስፋቷ ትልቋ አህጉር እስያ ናት፡፡
4. ኢትዮጵያ በአውሮፓ አህጉር ውስጥ ትገኛለች፡፡
5. ሁሉም አህጉራት እኩል የሆነ የቆዳ ስፋት አላቸው፡፡

**ማስታወሻ የዐረፍተ ነገርአወቃቀር/አመሰራረት/**

ዐረተፍተ ነገር ማለት በስርዓት ተቀነባብሮ ሙሉ መልዕክት ሊሰጥ የሚችል የሐረጎች ስብስብ ነው፡፡ዐረፍተ ነገር ሲዋቀር ሁለት ሐረጎችን በውስጡ ይይዛል፡፡

እነሱም፡- የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነው ክፍል ስማዊ ሐረግ ሲሆን የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ማብቂያ ክፍል የያዘው ግሳዊ ሐረግ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- አበበ መጣ፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር ሲሆን

ሀ. የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት -------- አበበ ነው፡፡

ለ. የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ግስ/--------መጣ የሚለው ቃል ነው፡፡

## ተግባር ሁለት፡-መጻፍ

ሀ. ተማሪዎች ከላይ በተሰጠው የዐረፍተ ነገር አወቃቀር ማስታወሻ መሰረት ከታች የተዘረዘሩትን ዐረፍተ ነገሮች ክፍሎቻቸውን ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ኤቢሴ ሄደች፡፡

ሀ. የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት -------- ነው፡፡

ለ. የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ግስ/-------- የሚለው ቃል ነው፡፡

2. ለሚ ሮጠ፡፡

ሀ. የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት -------- ነው፡፡

ለ. የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ግስ/-------- የሚለው ቃል ነው፡፡

3. እነ አብዲ ተናገሩ፡፡

ሀ. የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት -------- ነው፡፡

ለ. የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ግስ/-------- የሚለው ቃል ነው፡፡

4. እኛ እንጫወታለን፡፡

ሀ. የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት -------- ነው፡፡

ለ. የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ግስ/-------- የሚለው ቃል ነው፡፡

5. ኦብሴ ነይ፡፡

ሀ. የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት -------- ነው፡፡

ለ. የዐረፍተ ነገሩ መቋጫ/ግስ/--------መጣ የሚለው ቃል ነው፡፡

**ማስታወሻ፡- አንቀፅ**

ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ላይ በመጣመር አንቀጽ ይመሰርታሉ፡፡አንቀጽ ስለአንድ ሀሳብ የሚገልጽ አነስተኛ የጽሁፍ ክፍል ነው፡፡በአንድ ሀሳብ ዙሪያ የሚጻፍ ጽሁፍ ነው፡፡አንድ አንቀጽ ሲጻፍ በርካታም ይሁን ጥቂት ዓረፍተ ነገሮችን በውስጡ ሊይዝ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ላይ በማጣመር ወደ አንቀጽ እንዴት እንደሚቀየሩ እንመልከት፡፡

ሰዓዳ ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡

ዘወትር በርትታ ታጠናለች፡፡

የሚሰጣትን የቤት ስራም በጊዜ ሰርታ ታጠናቅቃለች፡፡

ለዚህም መምህሮቿ በጣም ይወዷታል፡፡

ይህ ሀሳብ ወደ አንቀጽ ሲቀየር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሰዓዳ ጎበዝ ተማሪ ስለሆነች ዘወትር በርትታ ታጠናለች፤ ስለዚህ የሚሰጣትንም የቤት ስራ በጊዜ ሰርታ ታጠናቅቃለች፤ ከዚህም የተነሳ መምህሮቿ በጣም ይወዷታል፡፡ (እንግዲህ ተማሪዎች ይህ ለአንድ አንቀጽ ምሳሌ ይሆናል)

ለ. ከላይ ስለአንቀጽ ምንነት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ከታች የተቀመጡትን ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ላይ በማቀናጀት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. ኬና ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡
2. ትምህርቱን በጣም ይወዳል፡፡
3. በፕሮግራም የማጥናት ልምድ አለው፡፡
4. ይህ ጉብዝናው ከክፍሉም አንደኛ እንዲወጣ አስችሎታል፡፡
5. በዚህም የተነሳ ትምህርት ቤቱና ወላጆቹ ለማበረታቻ የሚሆን ቦርሳና የእጅ ሰዓት ሸልመውታል፡፡

# ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ተግባር አንድ

ሀ. የቃላት ግንዛቤያችሁን ለማሳደግ ይረዳችሁ ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. ከትምህርት መሳሪያዎች መካከል አራቱን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ቦርሳ

ሀ.---------------

ለ.---------------

ሐ.--------------

መ.-------------

2. ከቤት እንስሳት መካከል አምስቱን ፃፉ።

ምሳሌ፡- በግ

ሀ.-----------------

ለ.-----------------

ሐ.----------------

መ.----------------

ሠ.----------------

3. ከዱር እንስሳት መካከል ቢያንስ የአምስቱን ስም ጻፉ።

ምሳሌ፡- ቀበሮ

ሀ.----------------

ለ.----------------

ሐ.---------------

መ.---------------

ሠ.---------------

ለ. ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጡትን ተዘውታሪ ቃላት አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሠላምታ መለዋወጥ

| ተ.ቁ | ለወንድ | ለሴት | ለብዙ | ለአክብሮት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ደህና አደርክ? | ደህና አደርሽ? | ደህና አደራችሁ? | ደህና አደሩ? |
| 2 | ደህና አረፈድክ? | | | |
| 3 | ደህና ዋልክ? | | | |
| 4 | ደህና አመሸህ? | | | |

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቦታ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከታዋቂ ቦታዎች መካከል ሶስቱን ጥቀሱ፡፡
3. ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን በክፍል ውስጥ ፊት ለፊት ወጥታችሁ ሠላምታ በስልክ ተለዋወጡ፡፡
4. የቃላት ግንዛቤያችሁን አሻሽላችሁ ከሆነ እንዴት እንዳሻሻላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
5. ቀጥሎ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ዐረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ አዋቅሩ፡፡

ምሳሌ፡- አበበ ሄደ ትምህርት ቤት ወደ

አበበ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

ሀ. አለሚቱ ታጠናለች ትምህርቷን በሚገባ

ለ. አቶ ወጡ አየለ ዛፍ ላይ

ሐ. ተማሪ ወጣ ጎበዙ ከክፍል አንደኛ

6. ዐረፍተ ነገሮችን በማቀናጀት አንቀጽ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
7. ተዘውታሪ የሆኑ ቃላትን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት
# የትራፊክ አደጋ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች�: -**

- አካል ጉዳተኝነት ከምን እንደሚመጣ አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ በማዛመድ ትናገራላችሁ፡፡
- የአካል ጉዳተኞችን እንዴት ልትረዷቸው እንደምትችሉ ተወያይታችሁ፡፡
- ረጅም ተግባቦትን ከመፍጠር አንፃር ስለራሳችሁ ሰፊ ንግግር ትናገራላችሁ፡፡
- የትራፊክ አደጋ እንዴት ሊደርስ እንደሚችል ትናገራላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ ታዛምዳላችሁ፡፡
- ባዶ ቦታውን በተስማሚው ቃል በመተካት ዓረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- ጥምር ቃላትን ከሁለት የተለያዩ ትርጉም ካላቸው ቃላት ትመሰርታላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ

## 1.ማዳመጥና መናገር

### 1.1.ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ

ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. አካል ጉዳተኝነት ከምን ሊመጣ ይችላል?
2. በመኪና መንገድ ላይ መጫወት የሚያመጣውን ጉዳት ተናገሩ፡፡

ለ. መምራችሁ ሲያነቡላችሁ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆነውን ሀሳብ ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ‹‹ሐሰት››በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው መማርና መስራት ይችላሉ፡፡
2. አካል ጉዳተኝነት በበሽታ ብቻ የሚመጣ ነው፡፡
3. ከባድ የመኪና አደጋ የአካል ጉዳተኝነትን ያስከትላል፡፡
4. አካል ጉዳተኞችን መርዳት ተገቢ ነው፡፡

ለ. በ‹‹ሀ››ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከ‹‹ለ››ረድፍ ከቀረቡት ጋር በፍች የሚመሳሰሉትን አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
| --- | --- |
| 1. የማየት እክል ያለባቸው | ሀ. መርዳት |
| 2. የመስማት እክል ያለባቸው | ለ. መስማት የማይችሉ |
| 3. ማገዝ | ሐ. ማየት የማይችሉ |
| 4. የተመጣጠነ ምግብ | መ. መሄድ ያለመቻል |
| | ሠ.ገንቢ ምግብ |

## 1.2. መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

1. የአካል ጉዳተኝነት በምን ምክንያት ሊመጣ ይችላል፡፡
2. አካል ጉዳተኞችን እንዴት ልትረዷቸው ትችላላችሁ?

ለ. የሚከተለውን ምሳሌ በመከተል ከጓደኞቻችሁ ጋር ስለ ራሳችሁ ተነጋገሩ።

ሰፊ/ረጅም /ተግባቦትን መፍጠር

ምሳሌ፡- እኔ ስሜ ሄኖክ ነው።

እድሜዬ ዘጠኝ አመት ነው።

የምኖረው ከወላጆቼ ጋር ነው።

አባቴ አሊ ይባላል። እናቴ ደግሞ ብዙነሽ ትባላለች።



አንድ ወንድምና አንድ እህት አሉኝ

በጣም እወዳቸዋለሁ

አሁን ወደ ትምህርት ቤት እየሔድኩ ነው።

የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። በትምህርቴ ጎበዝ መሆን እፈልጋለሁ።

# ክፍል ሁለት

## 2. ማንበብና መፃፍ

### 2.1. ማንበብ

የትራፊክ አደጋ

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

#### ተግባር አንድ

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተለውን ጥያቄ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡


1. የመኪና አደጋ እንዴት ሊደርስ ይችላል?
2. መንገድ ስንሻገር ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን?

## የትራፊክ አደጋ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የትራፊክ አደጋ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በመረጃው መሰረት ከሐምሌ 1/2002 እስከ ታህሳስ 30/2013ዓ.ም. ድረስ በደረሰው አደጋ አንድ ሺ ስምንት መቶ አርባ ዘጠኝ (1ሺ 849) ሰዎች ሞተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ብቻ ደግሞ መቶ ዘጠና ሁለት ሰዎች (192) ህይወታቸው አልፏል፡፡ በስምንት መቶ አርባ ስድስት (846) ሰዎች ላይ ከባድ በአምስት መቶ አስራሁለት (512) ሰዎች ላይ ቀላል ጉዳት ደርሷል፡፡

ለነዚህ አደጋዎች ደግሞ ምክንያት የተባሉት የአሽከርካሪዎች ቸልተኝነትና ብቃት ማነስ፣ የተሽከርካሪዎች ችግር፣ የመንገድ ስራ ችግርና የእግረኞች መንገድ አጠቃቀም ችግር ናቸው፡፡

በሰዎች ህይወት፣ በአካልና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሁላችንም ግራችን ይዘን መጓዝ ይጠበቅብናል። መንገድ ስናቋርጥ ለእግረኛ በተፈቀደው መሻገሪያ (ዜብራ) መንገድ ላይ ብቻ መጠቀም እና በመኪና መንገድ ላይ መጫወት አይገባንም። በአጠቃላይ ሌላውንም የትራፊክ ህግ አክብረን በመንቀሳቀስ ራሳችንን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ አለብን።



ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን ሀሳብ ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሐሰት››በማለት መልሱ፡፡

1. በመኪና መንገድ ላይ ኳስ መጫወት ለአደጋ ያጋልጣል፡፡
2. በሀገራችን ኢትዮጵያ የትራፊክ አደጋ እየጨመረ መጥቷል፡፡
3. መኪና የሚነዳ ሰው ጥንቃቄ ማድረግ የለበትም፡፡

ሐ. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. የትራፊክ አደጋ የሚመጣው በ----------------- ነው፡፡

   ሀ.በእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም ለ.በሹፌሮች ግዴለሽነት

   ሐ.በመንገድ ችግር መ.ሁሉም

2. በሀገራችን ኢትዮጵያ የትራፊክ አደጋ------------------

   ሀ.በጭራሽ የለም ለ. እየበዛ መጥቷል

   ሐ.አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል መ.ለእና ሐ መልስ ናቸው

3. በትራፊክ አደጋ ምክንያት ----------------

   ሀ. ሰው ይሞታል ለ. ንብረት ይወድማል

   ሐ. አካል ይጎላል መ.ሁሉም

4. የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስብን -------------------

ሀ. እራሳችንን መጠበቅ አለብን

ለ. የትራፊክ ህግን ማክበር አለብን

ሐ. መንገድ ስንሻገር ግራና ቀኝ ማየት አለብን

መ. ሁሉም

መ. ከዚህ በታች በ‹ሀ›ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ከ‹ለ›ረድፍ ከቀረቡት ጋር በፍች የሚመሳሰሉትን አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
| --- | --- |
| 1.የትራፊክ አደጋ | ሀ. በእግር የሚሄዱ ሰዎች |
| 2.እግረኞች | ለ. ጥንቃቄ የሌለው |
| 3.ብቃት ማነስ | ሐ. የመኪና አደጋ |
| 4. ግዴለሽነት | መ. የችሎታ አለመኖር |

## 2.2.መፃፍ

### ተግባር አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም በባዶ ቦታ ላይ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | |
|---|---|
| መጫወት | ሲያቋርጡ |
| ሞተዋል | መርዳት |
| ለአካል | ጉዳተኝነት |

1. ተማሪዎች መንገድ ----------------መጠንቀቅ አለባቸው፡፡
2. አካል ጉዳተኞችን ------------------ አለብን
3. በመኪና አደጋ ብዙ ሰዎች -----------------
4. በትምህርት ሰዓት ------------------ ተገቢ አይደለም፡፡
5. የመኪና አደጋ ------------------ይዳርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3.ቃላት

ማስታወሻ

ጥምር ቃላት ፡- ማለት ሁለት የተለያዩ ትርጉም ያላቸው ቃላት በአንድ ላይ ሆነው አንድ ለየት ያለ ትርጉም ሲሰጡ ነው።

ምሳሌ፡- ቤት + መፅሀፍ = ቤተ-መፅሀፍ

ወጥ + ቤት = ወጥ-ቤት

### ተግባር አንድ

ሀ. በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ቃላት አጣምራችሁ ፃፉ

1. ፀረ + ሙስና =---------------- 4. ህግ + ወጥ =---------------
2. ስነ + ስርዓት =--------------- 5. አመል + ወርቅ =-----------
3. ቤት + መንግስት = --------------

## የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር መልስ ስጡ።

1. ስነ + ዜጋ =------------------------
2. ቤት + ሙከራ =----------------
3. ፀረ + ኤድስ =---------------------
4. ልብ + ቢስ=----------------
5. አየር + መንገድ=-------------

# ምዕራፍ ስምንት
# ሥርዓተ ፆታ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ህፃናት መብታቸው ተጠብቆ ካደጉ ውጤታማ እንደሚሆኑ ትናገራላችሁ፡፡
- ለሀገር ጠቃሚ ዜጋን ማፍራት የሚቻለው ህፃናንት በመንከባከብ መሆኑን ትናገራላችሁ፡፡
- ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ጥያቄዎቹን በቃል ትናገራላችሁ፡፡
- የምትወዱትንና የማትወዱትን ነገር ለይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ሴቶች ከተማሩ ከወንዶች እኩል ማንኛውንም ስራ መስራት እንደሚችሉ ትናገራላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ ታዛምዳላችሁ፡፡
- ስለ ግብይት ሁኔታ የቀረበ ቃለ ምልልስ በቡድን ሆናችሁ በመፃፍ ታቀርባላችሁ፡፡
- የተዘበራረቁ ቃላትን በመገጣጠም ዓረፍተ ነገር ትፅፋላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ

## 1.ማዳመጥና መናገር

### 1.1.ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ

ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ለህፃናት ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤ ተዘርዝሩ፡፡
2. ህፃናት የነገ ሀገር ተረካቢ ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. መምራችሁ ሲያነቡላችሁ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆነውን ሀሳብ ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ‹‹ሐሰት››በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ህፃናት መብታቸው ተጠብቆ ካደጉ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡
2. ህፃናት የወላጅ ፍቅር የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3. ህፃናትን የመንከባከብ ሀላፊነት የወላጅ ብቻ ነው፡፡
4. ህፃናትን በስርዓት የማሳደግ ሀላፊነት የእናት ብቻ ነው፡፡
5. ለሀገር ጠቃሚ ዜጋን ማፍራት የሚቻለው ህፃናትን በመንከባከብ ነው፡፡

### ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሆነውን በመምረጥ መልሱ።

1 ህፃናት-------------- የማወቅ መብት አላቸው።

ሀ. ወላጆቻቸውን ለ. ህዝቡን ሐ. ማንንም መ. ሁሉም

2. ሁሉም ህፃናት -----------------መብት የላቸውም።

ሀ. የመናገር ለ. የመሳደብ ሐ.የመጫወት መ. የመማር

3. ወላጆች----------------የማሳደግ ሀላፊነት አለባቸው።

ሀ.ልጆቻቸውን ለ.ህፃናትን

ሐ.ሀእናለ መ.ሁሉም

4. አካል ጉዳተኛ ህፃናት እንደማንኛውም ህፃን ---------------- አላቸው።

ሀ. የቤተሰብ ፍቅር ለ. መብት

ሐ. ህይወት መ. ሁሉም

5. የጉልበት ብዝበዛ ማለት-------------

ሀ. ያለዕድሜያቸው ልጆችን ስራ ማሰራት ለ. ለልጆች እረፍት መስጠት

ሐ. ልጆችን እንዲማሩ ማድረግ መ. ልጆች ፍቅር እንዲያገኙ ማድረግ

## 1.2. መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

1. ከፍራፍሬ አይነቶች ውስጥ የምትወዱትን መርጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ከምትወዱት የቤት እንስሳት ውስጥ ሶስቱን ተናገሩ።

# ክፍል ሁለት

## 2. ማንበብና መፃፍ

### 2.1. ማንበብ

ሥርዓተ-ጾታ

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

### ተግባር አንድ

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተለውን ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ።

1. ሴቶች በቤት ውስጥ ያላቸውን ሀላፊነት ተናገሩ።
2. በቤት ውስጥ ሴቶችና ወንዶች ልጆች እኩል መብት አላቸው።

## ሥርዓተ - ጾታ

በህብረተሰባችን ውስጥ ለሴት ልጆችና ለወንድ ልጆች የሚሰጠው ግምት እኩል መሆን አለበት፡፡ በቤት ውስጥ ወላጆች ወንዶች ልጆችን ጎበዝ ሴት ልጆችን ሰነፍ አድርገው መቁጠር የለባቸውም፡፡

ሴቶች ከወንዶች እኩል በመሆናቸው ለወንዶች የምናደርገውን ማንኛውንም አይነት እንክብካቤና ድጋፍ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር፣ የመጫወት፣ በቤት ውስጥም በወላጆቻቸው የመወደድና ነፃነት የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ሴቶች ብዙ ሀላፊነት ስላለባቸው መማር የሚገባቸውን ያህል ለማስተማር ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ እድገት የሚኖረው በትምህርት ነው፡፡ ሴቶች ደግሞ የመማር እድሉን ካገኙ በራሳቸው ተማምነው የመኖር ብቃት ይኖራቸዋል፡፡ ከኋላ ቀር አስተሳሰብ ይላቀቃሉ፡፡

ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን ሀሳብ ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሐሰት››በማለት መልሱ፡፡

1. ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እድገት የሚያገኙት በትምህርት ነው፡፡
2. ሴቶች ልጆች እንደ ወንድ ልጆች የመማር መብት አላቸው፡፡
3. ሀገር የምታድገው በወንዶች መማር ብቻ ነው፡፡
4. ሴቶች የሀላፊነት ስራን መስራት ይችላሉ፡፡
5. በህብረተሰባችን ውስጥ የሴቶች ስራ ትንሽ ነው፡፡

ሐ. በ‹‹ሀ››ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ‹‹ለ››ረድፍ ከቀረቡት ቃላት ጋር ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ብዙ | ሀ. መጠላት |
| 2. ወንድ | ለ. ማጣት |
| 3. መወደድ | ሐ. ዝቅተኛ |
| 4. ማግኘት | መ. ሴት |
| 5. ከፍተኛ | ሠ. ትንሽ |

## 1.2 መፃፍ

ማስታወሻ

አንድን እቃ የመሸጥ ወይም የመግዛት ሂደት ግብይት ይባላል። ለምሳሌ ቅቤ፣ ስኳር፣ ቡና፣ ልብስና የመሳሰሉትን መሸጥና መግዛት ግብይት ይባላል።

ምሳሌ፡-ስለ ግብይት የቀረበ ጭውውት

ገዢ፡-ባለ ቅቤ!

ባለ ቅቤ፡- አቤት!

ገዢ፡- ሁለት ኪሎ ቅቤ ለቅዳሜ አምጣልኝ።

ባለ ቅቤ፡- እሺ!

ገዢ፡- አደራህን! አደራህን!

ባለ ቅቤ፡- ‹‹ምን ሆነሃል ግድ የለም እያልኩህ››

ገዢ፡- አደራ! ያልኩህ ለምን እንደሆነ አላወክም?

ባለ ቅቤ፡- ለምንድ ነው?

ገዢ፡- በዓል እየመጣ ስለሆነ ነው።

### ተግባር አንድ

ሀ. በቡድን ሆናችሁ በመወያየት ስለ ግብይት የቀረበ ጭወውት በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ክፍል ሶስት

## 3. ቃላት

### ተግባር አንድ

ሀ. ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት በመገጣጠም ዓረፍተ ነገር ስሩ።

ምሳሌ፡- አያንቱ ደብተር ገዛች።

| | | |
|---|---|---|
| እኔ | እርሳስ | መጣ |
| አያንቱ | ምግብ | በላ |
| ልጁ | ደብተር | አለኝ |
| ከድር | በጠዋት | ነው |
| ጫላ | ትልቅ | ገዛች |

1. --------------------
2. -------------------
3. ------------------
4. -------------------

## የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ.የሚከተሉትን ቃላት በማገጣጠም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. ገባሁ / ቤት / ትምህርት፡፡
2. ነው / ቤታችን / ሰፊ፡፡
3. ለበሰች / ቀሚስ / ቀይ፡፡
4. ሁል ጊዜ / እኔ / አጠናለሁ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የታዋቂ ሰው ታሪክ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ባዳመጡት ምንባብ መሰረት እራሳቸውን ይገልፃሉ፡፡
- የንግግር ርእሶችን ተጠቅመው ይናገራሉ፡፡
- የተመረጡ ታሪኮችን ይናገራሉ፡፡
- ስለማጠቃለያና ዋና ሀሳብ ምንነት ይናገራሉ፡፡
- ስለታዋቂ ሰው ታሪክ ያነባሉ፡፡
- ረጃጅም አንቀፆችን አንብበው ይረዳሉ፡፡
- ዝምድናን የሚገልፁ ስሞችን ያነባሉ፡፡
- ሐረጋትን ለይተው ይፅፋሉ፡፡

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## ተግባር አንድ፡-ማዳመጥ

ሀ. ራስን መግለፅ በሚል መምህራችሁ ባነበቡላችሁ ምንባብ መሰረት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ “እውነት” ስህተት ከሆነ ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

1. ኢንጂፈኖ የሚኖረው ብቻውን ነው፡፡
2. የኢንጂፈኖ እድሜ አስራ አምስት ነው፡፡
3. ኢንጂፈኖ ወንድምና እህቶቹን ይወዳል፡፡
4. ኢንጂፈኖ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡
5. ኢንጂፈኖ ሰነፍ ተማሪ ስለሆነ ትምህቱን አይወድም፡፡
6. ኢንጂፈኖ ለወደፊት ዶክተር መሆን ይፈልጋል፡፡

## ተግባር ሁለት፡- መናገር

ሀ. ከላይ በመምህር መምሪያ ላይ ራስን መግለፅ በሚል ፅሁፍ ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት እናተም ተራ በተራ በመነሳት ራችሁን ግለፁ፡፡

### ማስታወሻ፡- ንግግር

ንግግር ማለት ስለ አንድ ጉዳይ ለሌሎች አድማጮች መልዕክት ማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡የንግግር ችሎታን ለማዳበር ደጋግሞ መናገር ጥሩ ይሆናል፡፡ለዚህ ሁኔታ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት ደግሞ አመቺ ሁኔታ፣የመኖሪያ ቦታ ወይም አመቺ መድረክ፣የአድማጭ መኖር የመሳሰሉት ናቸው፡፡ሌሎች ሲናገሩ ጥሩ አድማጭ ሆኖ መገኘትም የንግግር ችሎታን ለማዳበር የሚረዳን ጉዳይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሆነው በራስ መተማመን ማጎልበት ነው፡፡ በራስ በመተማመን በመድረክ ላይ እንድንናገር ያበረታታናል፤ተሳታፊም ያደርገናል ማለት ነው፡፡በንግግር መሳተፍ ደግሞ ለማዳመጥም ሆነ ለመናገር ይጠቅመናል፡ የቋንቋ ችሎታን ያዳብራል፡፡

ለ. ስለንግግር ምንነት ከላይ በተሰጣችሁ ማስታወሻ መሰረት ከተሰጡት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል መርጣችሁ በክፍል ውስጥ ንግግር አድርጉ፡፡

1. ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች
2. ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ መንገዶች
3. ስለተማሪዎች መብት
4. ስለተማሪዎች ግዴታ
5. ስለትራፊክ ህጎች

ሐ. ከዚህ በታች የተመረጠ ታሪክ ቀርቦላችኋል፡፡ እናንተም በታሪኩ መሰረት የምታውቁትን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ታሪኩና በቀለ

ታሪኩና በቀለ ጓደኛሞች ናቸው፡፡

የሚኖሩት በድሬዳዋ ከተማ ነው፡፡ ሁል ጊዜ አብረው ያጠናሉ፡፡የሚከብዳቸውን ስራ በመተጋገዝ ይሰራሉ፡፡ በእረፍት ጊዜያቸው ደግሞ ኳስ ይጫወታሉ፡፡ ታሪኩ እድሜው አስር ዓመት ነው፡፡ በቀለ ግን አስራ አንድ ዓመቱ ነው፡፡ ቁመታቸው ግን እኩል ነው፡፡ የታሪኩና የበቀለ አባቶች ጓደኛማቾች ናቸው፡፡ በጣም ይዋደዳሉ፡፡ በዓመት በዓል ጊዜ በዓሉን በጋራ ያከብራሉ፡፡


ማስታወሻ፡-ዋና ሐሳብና ማጠቃለያ

ዋና ሐሳብ፡- ስለአንድ ጉዳይ መነሻ ወይም መንደርደርያ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ደግሞ በዝርዝር ማብራሪያ መቅረብ ይችላል፡፡ በዝርዝር የቀረበው ማብራሪያም በማጠቃለያ ሀሳብ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ስለዚህ ዋና ሀሳብ በአንድ ፅሁፍ ውስጥ በመጀመሪያ ላይ፣መጨረሻ ላይ፣ መሃል ላይ፣መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ሊመጣ ይችላል፡፡

ማጠቃለያ፡-ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር ሐሳቦች ከቀረቡ በኋላ በዝርዝር የቀረበውን ሀሳብ ዋና ዋና ትኩረት የምንመለከትበት ክፍል ነው፡፡

መ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በመፅሃፉ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች በመመልትከት ዋና ሐሳቡን እና ማጠቃለያውን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ በታች ያለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት እነዚህን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ታዋቂ ሰዎች ስም ተናገሩ፡፡
2. ታዋቂ ለመሆን ምን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. እናንተ ታዋቂ የመሆን ፍላጎት አላችሁ? በምን መታወቅ ትፈልጋላችሁ?

## ጌጤ ዋሚ

ጌጤ ዋሚ ተወልዳ ያደገችው በደብረ ብርሃን አውራጃ ጫጫ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ነው፡፡ ወደ ሩጫ ስፖርት ስትገባ ከቤተሰብና ከአካባቢዋ ጠንካራ ተቃውሞ ነበር የገጠማት፡፡ ባህሉ ሴት ልጅ በአደባባይ ሙያ እንድትሳተፍ የማይፈቅድ በመሆኑ ከፍተኛ ጫና ይደርስባት ጀመር፡፡ ነገር ግን በእምቢተኛነቷ በመፅናት በቆራጥነት ስፖርቱን ቀጠለች፡፡ ከብዙ ጥረት በኋላ የተለያዩ ውድድሮችን በማድረግ ማጣሪያዎችን አልፋ አዲስ አበባ በመምጣት በ1982 ዓመት ምህረት ኦሜድላ ክለብ ገባች፡፡ በቀጣይ ዓመት የአለም አቀፍ ውድድሮችን ለመካፈል በሚያበቃው የጃን ሜዳ የስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ውድድር ተካፍላ ሶስተኛ በመውጣት በዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና ውድድር ተካፋይ ለመሆን ቻለች፡፡



## ተግባር አንድ፡- ማንበብ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. ጌጤ ዋሚ ኦሜድላ ክለብን የተቀላቀለችው በስንት ዓመተ ምህረት ነው?

   ሀ. 1992 ለ.1982 ሐ. 1996 መ. 1984

2. ጌጤ ዋሚ በጃንሜዳ የስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ውድድር በተካፈለችበት ወቅት ስንተኛ ወጣች?

   ሀ. ሁለተኛ ለ. አንደኛ ሐ. ሶስተኛ መ. አራተኛ

3. ጌጤ ዋሚ በ__________ሻምፒዮና ውድድር ተካፋይ ለመሆን ቻለች።

   ሀ. በወረዳ ለ. በዞን ሐ. በአገር መ. በዓለም

4. ጌጤ ዋሚ በየትኛው የስራ መስክ ትታወቃለች?

   ሀ. የሩጫ ስፖርት ለ. ህክምና ሐ. ንግድ መ. ውድድር

5. ጌጤ ዋሚ ወደ ሩጫ ስፖርት ስትገባ ጠንካራ ተቃውሞ የገጠማት ከማን ነው?

   ሀ. ከቤተሰብ ለ. ከአካባቢ ሐ. ከባለቤቷ መ ሀ እና ለ

ለ. በምዕራፍ ስድስት ስለ አንቀፅ ምንነት መማራችሁን ታስታውሳላችሁ፡፡ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ አንብቡና የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡

ምሳሌ አንድ

## የቤተ መፅሐፍት ህጎች

የክፍል ትምህርት ብቻ ለተማሪዎች በቂ አይደለም፡፡በክፍል ከሚማሩት ትምህርት በተጨማሪ ሌሎች መፃህፍትን በማንበብ እውቀታቸውን ማስፋት ይኖርባቸዋል፡፡ለዚህም ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው ወደ ቤተ መፃህፍት በመግባት ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ወደ ቤተ መፅሐፍ ሲሄዱም ደንቡን ማወቅና ማክበር ተገቢ ነው፡፡ሊከበሩ ከሚገባቸው የቤተ መፃህፍት ህጎች መካከል ግንባር ቀደሞቹ ከእስኪርብቶና ከማስታወሻ ደብተር በስተቀር ሌላ ነገር አለመያዝ፣ሲያነቡ ድምጽ አለማሰማት፣ከሌሎች ጋር አለማውራት፣እርዳታ ሲፈልጉ የቤተ መፃህፍቱን ሠራተኞች ቀስ ብሎ መጠየቅ፡፡

ምሳሌ ሁለት

## የትምህርት ቤት ህጎች

ተማሪዎች በክፍል አለቃቸው አማካኝነት የክፍል ፅዳት ፕሮገራም ያወጣሉ፡፡ በወጣው ፕሮግራም መሰረት በየቀኑ ሁለት ሁለት ተማሪዎች ክፍል ያፀዳሉ፡፡ ቆሻሻውን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ይጨምራሉ፡፡ክፍላቸውን ሁል ጊዜ በንፅህና ስለሚይዙ ጤንነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፋቸውን በመሸፈን በንፅህና መያዝ ይገባቸዋል፡፡ በዓመቱ መጨረሻም የመፅሐፉ ንፅህና እንደተጠበቀ ለትምህርት ቤቱ ይመለሳል፡፡ቀጣይ ተማሪዎችም በንፅህና ጠብቀው ይጠቀሙባቸዋል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ፣መምህራንና ታላላቆቻቸውን ማክበር ይገባቸዋል፡፡እንደዚሁም ጓደኞቻቸውንም ማክበርና መውደድ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ሲያደርጉ እነሱም ይወደዳሉ፤ይከበራሉ፡፡

ለ. ከዚህ በላይ ስለአንቀፅ የተሰጠውምን ምሳሌ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የቤተ መፃህፍት ህጎች የሚለው ሃሳብ በስንት አንቀፅ የቀረበ ነው?
2. የቤተ መፃህፍት ህጎች የተሰኘው ሀሳብ የቀረበው በረጅም አንቀፅ? ወይስ በአጭር? ለመምህራችሁ ንገሯቸው።
3. የትምህርት ቤት ህጎች የተገለፀበት ሐሳብ በስንት አንቀፆች የቀረበ ነው?
4. የትምህርት ቤት ህጎች የሚለው አንቀፅ የቀረበው በረጅም አንቀፅ ወይስ በአጭር አንቀፅ ነው?
5. በቤተ-መፃህፍት ውስጥ መከበር ያለባቸውን ደንቦች ዘርዝሩ።
6. በትምህርት ቤት ውስጥ መከበር ያለባቸውን ደንቦች ተናገሩ።
7. በመማሪያ መፅሐፋችሁ ውስጥ በቀረቡት ምንባቦች መሰረት የቀረቡትን አንቀፆች በማየት አጫጭር፣መካከለኛና ረጃጅም አንቀፅ መሆናቸውን በመለየት ለመምህራችሁ ንገሩ።

ሐ. ቀጥሎ የቀረቡትን ዝምድናን የሚገልፁ ስሞች አንብቧቸው፡፡

1. አባት
2. እናት
3. ወንድም
4. እህት
5. አጎት
6. አክስት
7. አያት
8. ቅድመ አያት

## ተግባር ሁለት፡- መፃፍ

ሀ. ከዚህ በፊት በተማራችሁት መሠረት ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላትና ሐረጋት መካከል ሐረጋት የሆኑትን ብቻ ለይታችሁ በባዶ ቦታ ላይ ፃፉ፡፡

ሀ. መኪና መንዳት
ለ. ቦርሳ
ሐ. ቤት መስራት
መ. ወረቀት
ሠ. ከትምህርት ቤት
ረ. ልብስ ማጠብ
ሰ. ኳስ
ሸ. ኳስ መጫወት
ቀ. ወደ ቤቱ
በ. ትምህርት መማር
ተ. ከእረፍት መልስ
ቸ. መጽሐፍ
ኀ. ስፖርት መስራት
ነ. ልብሱን ለብሶ

1. ________________
2. ________________
3. ________________
4. ________________
5. ________________
6. ________________
7. ________________
8. ________________
9. ________________
10. ________________

# ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ተግባር አንድ

**ሀ. በ ‹‹ሀ›› ስር ያሉትን ቃላት በ ‹‹ለ›› ስር ካሉት ቃላት ጋር በተቃራኒ ፍቺያቸው አዛምዱ፡፡**

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ይበልጣል | ሀ. ቅርብ |
| 2. ሄደ | ለ. መጣ |
| 3. ወደደ | ሐ. ያንሳል |
| 4. ሩቅ | መ. ጠላ |
| 5. ከፊት | ሠ. አስተማሪ |
| 6. ተማሪ | ረ. ከኋላ |

**ለ. ተገቢ የሆኑ ቃላትንና ሐረጋትን መርጣችሁ ክፍት ቦታዎችን አሟሉ፡፡**

ምሳሌ፡- ጎበዝ ተማሪዎች አቅደው ይሰራሉ፡፡

ጊዜ ይለግሳሉ አቅደው

ዕቅድ መንፈቅ ዓመት

1. ተማሪዎች የጥናት---------------- ሊኖራቸው ይገባል፡፡
2. የአንደኛው---------------- ፈተና በጥር ወር ይሰጣል፡፡
3. በወጣው --------------- መሠረት በመስራት ውጤታማ ሆነ፡፡
4. በጎ አድራጊዎች ለተቸገሩ ሰዎች ገንዘብ ---------------፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ስለራሳችሁ የህይወት ታሪክ ተናገሩ፡፡
2. ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ንግግር አድርጉ፡፡
3. ስለምታውቁት ታሪክ በክፍል ውስጥ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
4. ዝምድናን የሚገልፁ ስሞችን ዘርዝሩ፡፡
5. አምስት ሐረጋትን ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ አስር
# ተረት

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የተረትን ምንነት ትናገራላችሁ፡፡
- ስለንግግር መመሪያ ምንነት ተረድታችሁ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- የተለያዩ አባባሎችን ትናገራላችሁ፡፡
- ተረቱን አንብባችሁ መልዕክቱን ትረዳላችሁ፡፡
- በተረቱ ውስጥ የተካተቱትን ገፀ ባህሪያትና ተግባራቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- በአንቀፅ ውስጥ ካሉ ሃሳቦች ለምን እና እንዴት የሚሉትን በምክንያት እና በውጤት የተጣመሩ ሃሳቦችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የአጭር አንቀፅ መልዕክትን ትረዳላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡-ማዳመጥና መናገር

### ተግባር አንድ፡- ማዳመጥ

ሀ. መምህራችሁ በመምህሩ መምሪያ ላይ ‹‹የተረት ምንነት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ማብራሪያ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተም ባዳመጣችሁት መሠረት ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎቸ መልሱ፡፡

1. ተረት ምንድ ነው?
2. ተረት መቼ መቼ ይነገራል?
3. ከስነ-ቃል አይነቶች ሶስቱን ተናገሩ፡፡
4. ተረት በማን እና በማን መካከል ይነገራል?
5. የተረት ደራሲዉ ማን ነው?

ለ. ያዳመጣችሁትን ፅሁፍ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሑፍ መልሱ፡፡

1. ከስነ-ቃል አንዱ---------ነው?

ሀ. ተረት ለ.ፊልም ሐ. ድራማ መ. ሁሉም

2. ተረት ሲነገር ምን ያስፈልጋል?

ሀ. አድማጭ ለ. ተናጋሪ ሐ. ማስታወሻ መ. ሀ እና ለ

3. በተረት ውስጥ ተካተው የሚጫወቱ ፍጥረታት--------ይባላሉ?

ሀ. ሰዎች ለ. እንስሳት ሐ. ገፀ-ባህሪያት መ. ሁሉም

4. የተረት ደራሲው ማን ነው?

ሀ. ግለሰብ ለ. ማህበረሰብ ሐ. አይታወቅም መ. ሁሉም

5. ተረት መቼ መቼ ይነገራል?

ሀ. ጠዋት ለ. ማታ ሐ. ቀን ላይ መ. ሰዓት የለውም

ማስታወሻ፡- የንግግር መመሪያ

አንድ ሰው ንግግር ከማድረጉ በፊት ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

ርዕስ መምረጥ

ዋና ዋና ሃሳቦችን በማስታወሻ ደብተር ላይ መጻፍ

ቅደም ተከተሉን ማስተካከል

ልምምድ ማድረግ

ተራ በተራ ፊት ለፊት በመውጣት ንግግር ማድረግ

## ተግባር ሁለት፡- መናገር

ሀ. ከላይ የቀረበውን የንግግር መመሪያ መሰረት በማድረግ ከታች ከተሰጡት ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ተራ በተራ ንግግር አድርጉ፡፡

ሀ. የህፃናት መብት

ለ. የወላጅ ሃላፊነት

ሐ. የትምህርት አስፈላጊነት

### ማስታወሻ፡- ልዩ ልዩ አባባሎች

አባባሎች በተለያየ መልኩ ሀሳባችንን ለመግለጽ የሚያስችሉን ናቸው፡፡ እነሱም፡- ከአንድ ድርጊት ጋር የተያያዙ አባባሎች፣ከእንስሳት ጋር የተያያዙ፣ ማድረግን፣ ብሎ፣ አለ፣ በል የሚሉትን አባባሎች፣ ድግግማዊ አባባሎችን በማለት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

- የደብዳቤ አፃፃፍ
- የቡና አፈላል
- የህልም አፈታት እና ሌሎችንም

2. ከእንስሳት ጋር የተያያዙ አባባሎች

❖ የኤሊ ጉዞ

❖ የዝሆን ጆሮ

❖ የዶሮ አይን

3.‹‹አድርግ›› የሚለውን የሚያስከትሉ አባባሎች

❖ ላስ አድርግ

❖ ሙልጭ አድርግ

❖ ቃም አድርግ

❖ ዋጥ አድርግ

4.‹‹ብሎ›› የሚለውን የሚያስከትሉት

❖ ዝቅ ብሎ

❖ ሳቅ ብሎ

❖ ፍጥጥ ብሎ

❖ አፈር ብሎ

5.‹‹አለ›› የሚለውን የሚያስከትሉ

- ክፍ አለ
- ክው አለ
- ዝም አለ
- ዘው አለ
- ድርቅ አለ

6.‹‹በል›› የሚለውን የሚያስከትሉት

- ፉት በል
- ዝም በል
- ጥርግ በል
- ክፍ በል
- ዝቅ በል
- ፈታ በል

7. ድግግማዊ አባባሎች

- ❖ ዱብ ዱብ
- ❖ ሮጥ ሮጥ
- ❖ ላስ ላስ
- ❖ ጫን ጫን

ለ. ከላይ ስለልዩ ልዩ አባባሎች የቀረበውን ማስታወሻና ምሳሌውን መሠረት በማድረግ ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከድርጊት ጋር የተያያዙ አባባሎችን የሚያመለክተው የቱ ነው?

ሀ. የኤሊ ጉዞ  ለ. የቡና አፈላል  ሐ. ጫን ጫን  መ. ዝቅ ብሎ

2. ‹‹አለ›› ከሚለው ቃል ጋር የማይሄደው አባባል የቱ ነው?

ሀ. ከፍ  ለ. ዝቅ  ሐ. የደብዳቤ አፃፃፍ  መ. ሳቅ

3. ድግግማዊ አባባል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ድርቅ አለ  ለ. ላስላስ  ሐ. ከፍ በል  መ. ዋጥ አድርግ

4. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ <<አድርግ>> የሚለውን አባባል የሚያስከትለው የትኛው ነው?

ሀ. አስፋፈር  ለ. ቃም  ሐ. ዋጥ  መ. ላስ

5. ከእንስሳት ጋር የተያያዘ አባባል ያልሆነው ነው?

ሀ. የኤሊ ጉዞ ለ. ዝቅ ብሎ ሐ. የዝሆን ጆሮ መ . የዶሮ ዓይን

6. ‹‹በል›› የሚለውን አባባል የሚያስከትለው የቱ ነው?

ሀ. ዝም ለ. ጥርግ ሐ. ዝቅ መ. ሁሉም መልስ ነው

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ተረት ምንድን ነው፡፡
2. ከዚህ በፊት ተረት ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?የምታስታውሱትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. ተረት አብዛኛውን ጊዜ በምን በምን ተመስሎ ይነገራል?

## ውሻና የሚያናፋው አህያ

በአንድ ወቅት የአንድ ሰው ንብረት የነበሩት አንድ ውሻና አንዲት አህያ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ከዕለታት አንድ ቀን ታዲያ ውሻው አህያዋን እንዲህ አላት፡፡

‹‹ሌሊት ሌሊት እየጮህኩ የጌታዬን ንብረት መጠበቅ ሰልችቶኛል፡፡››

አህያም እንዲህ ብላ አማረረች ‹‹እኔም ጌታዬ ወደ ገበያ በሄደ ቁጥር ከባድ ጭነት መሸከም ሰልችቶኛል፡፡ታዲያ ምን ብናደርግ ይሻላል?››

በመጨረሻም ቤታቸውን ጥለው ለመጥፋት ተስማምተው ተሰደዱ፡፡እየተጓዙም ሳለ በጣም ለምለምና ውሃ ያለው ሜዳ አጠገብ ደረሱ፡፡አህያዋ የምትበላውና የምትጠጣው ነገር አግኝታ ስትጠግብ ውሻው ምንም አላገኘም፡፡

እናም አህያዋ ከጠገበች በኋላ ‹‹አሁን ማናፋት አለብኝ››አለች፡፡ ውሻውም አህያዋ እንዳታናፋ እንዲህ ብሎ መከራት ‹‹ካናፋሽ የመጀመሪያው ድምፅ ጅቡን ይቀሰቅሰዋል፣ሁለተኛውም ድምፅ ያለንበትን ቦታ ይጠቁመዋል፣በሶስተኛውም አንቺን ይበላሻል፡፡››

አህያዋም ምክሩን ችላ ብላ አናፋች፡፡ጅቡም ድምጧን ሰምቶ በመምጣት አህያዋን መብላት ጀመረ፡፡

ጅቡም አህያዋን እየበላ ሳለ ውሻው ስጋውን እየቆረጠ ያቀርብለት ነበር፡፡ታዲያ ጅብ ውሻውን ‹‹የአህያዋን ልብ ስጠኝ፡፡›› ቢለው ውሻው አህያዋ ልብ የላትም፡፡ልብ ቢኖራትማ ኖሮ ባላናፋች ነበር፡፡ አለው ይባላል፡፡በተለምዶ ልብ የብልህነት መገኛ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ስለዚህ ምክር አለመስማት ለመጥፎ ነገር እንደሚዳርግ አውቃችሁ የሚነገራችሁን ምክር ተቀበሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡-ማንበብ

ሀ. ከላይ ያነበባችሁትን ተረት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የተረቱን መልዕክት ለመምህራችሁ በቃል ንገሯቸው፡፡
2. በተረቱ ውስጥ የተካተቱት ገፀ ባህሪያት እነማን ናቸው?ዘርዝሯቸው፡፡
3. ከላይ ባነበባችሁት ተረት ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪያት ተግባር ተናገሩ፡፡

ለ. በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ‹‹ሐሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ሌሊት ሌሊት እየጮሁኩ የጌታዬን ንብረት መጠበቅ ሰልችቶኛል ያለው ውሻ ነው፡፡
2. ጌታዬ ወደ ገበያ ሲሄድ ጭነት መሸከም አቅቶኛል ያለው አህያ ነው፡፡
3. ውሻ የአህያን ምክር አልሰማም ብሎ ማናፋት ጀመረ፡፡
4. ጅብ ለውሻው ስጋ እየቆረጠ ያቀርብ ነበር፡፡
5. ውሻና አህያ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡

## ተግባር ሁለት፡- መፃፍ

**ሀ. ባዶ ቦታውን ከምንባቡ ከተወጣጡት ቃላት በመምረጥ አሟሉ።**

ውሻም    አህያም    አናፋች    ልብ    ጅብ

1. ___________ሌሊት ሌሊት እጮሀለሁ አለ።

2. ___________ወደ ገበያ ስሄድ ከባድ ጭነት እሸከማለው አለ።

3. አህያዋ ምክሩን ችላ ብላ___________።

4. ___________የብልህነት መገኛ ነውተብሎ ይታመናል።

5. ___________ድምጧን ሰምቶ በመምጣት አህያዋን መብላት ጀመረ።

### ማስታወሻ፡- መንስኤና ውጤት

የአድማጭንም ሆነ የአንባቢን ስሜት ለማርካት የሚነገሩ ሐሳቦች በመንስኤና ውጤት የተጣመሩ ሊሆኑ ይገባል። በመንስኤና ውጤት ያልተጣመሩ ሐሳቦች የተሟሉ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ስለማይችሉ በአድማጩ ዘንድ ጥያቄን ያስነሳሉ።

ለምሳሌ፡- ‹‹ኢጃራ ሞተ፤ባለቤቱ ለሊሴም።›› በሚል ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ሰዎች መሞታቸው ተገልጧል። ነገር ግን ሁለቱ ሰዎች እንዴት ሊሞቱ እንደቻሉ ሐሳቡ በመንስኤና ውጤት አልተጣመረም።አድማጩም ከንግግሩ ወይም ከፅሁፉ ምላሽ ሊያገኝ ባለመቻሉ ጥያቄ ይፈጥርበታል፤እርካታም አይኖረውም።ስለዚህ ከላይ የቀረበው ሀሳብ በመንስኤና ውጤት ተጣምሮ መቅረብ ይኖርበታል።

‹‹ኢጃራ በኤች አይቪ/ኤድስ ሞተ። ባለቤቱ ለሊሴም በዚሁ በሽታ ታማ ሞተች። ቢባል አድማጩ ለሁለቱም ሰዎች መሞት መንስኤ/ምክንያቱ ኤች አይቪ/ኤድስ መሆኑና ውጤቱ ደግሞ ሞት መሆኑን ይረዳሉ።ስለዚህ ንግግሩ ለምን ሞቱ ወይም በምን ምክንያት ሞቱ?›› የሚል ጥያቄ አይፈጥርባቸውም። መንስኤና ውጤቱ ስለተጣመረ።

ለ. ከዚህ በላይ በተሰጠው ማስታወሻ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች መንስኤና ውጤት ለይታችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- ሀዊ በርትታ ስላጠናች ጥሩ ውጤት አመጣች፡፡

ሀ. መንስኤ--በርትቶ ማጥናት

ለ. ውጤት--ጥሩ ውጤት ማምጣት

1. ህፃኑ የፈላ ውሃ ተደፍቶበት እጁ ነፈረ፡፡

ሀ.መንስኤ፡-

ለ. ውጤት፡-

2. ሰውየው ሰክሮ ድንጋይ ላይ ወደቀ፡፡

ሀ.መንስኤ፡-

ለ. ውጤት፡-

3. ልጁ ሳያጠና ቀርቶ ፈተናውን ወደቀ፡፡

ሀ. መንስኤ፡-

ለ. ውጤት፡-

4. አሊ ቁርሱን ስላልበላ ራበው፡፡

ሀ. መንስኤ፡-

ለ. ውጤት፡-

ሐ. ከታች በቀረበላችሁ አጭር አንቀፅ መሠረት ከተሰጡት ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ውሃ

ውሃ ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ነው፡፡እንስሳትና ዕፅዋት ለመኖር ውሃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ያለ ውሃ ምንም አይነት ሕይወት የለም፡፡

1. ፀሐይ
2. አየር
3. አፈር

# ክፍል ሶስት፡-ቃላት

## ተግባር አንድ

### ሀ. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት መደቡን ጥቀሱ፡፡

ምሳሌ፡- እንጀራ በላ፡፡ 3ኛ መደብ

1. ፈተና አለፉ፡፡_______
2. ደስ ብሎናል፡፡_______
3. በርትተህ አጥና፡፡_______
4. ወሬ ትወዳለች፡፡_______
5. ግቡና ተኙ፡፡_______
6. ቁርስ በልተናል፡፡_______

### ለ. በምሳሌው መሠረት ሰንጠረዡን አሟሉ

| ቃል | ፆታ | መደብ | ቁጥር |
|---|---|---|---|
| አንተ | ወንድ | ሁለተኛ | ነጠላ |
| እነሱ | | | |
| እኔ | | | |
| እናንተ | | | |
| እሷ | | | |
| አንቺ | | | |
| እኛ | | | |

### ሐ. በ‹‹ሀ›› ሥር የቀረቡትን አባባሎች በ‹‹ለ›› ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ።

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. የቡና | ሀ. ጆሮ |
| 2. የኤሊ | ለ. ዓይን |
| 3. የዝሆን | ሐ. አፈላል |
| 4. የዶሮ | መ. አፈታት |
| 5. የህልም | ሠ. ጉዞ |

### መ. ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላት በተገቢው ባዶ ቦታ ላይ ሙሉ።

ቡድን ይደራጃሉ በንቃት ቤተ-መፅሐፍት

መንገድ ታጠናለች ተቋማት

1. ሰዎች በተለያዩ ማህበራት ______________ ።
2. በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ______________ ይሳተፋሉ።
3. በከተማው ውስጥ የተለያዩ የትምህርት ______________ አሉ።
4. ተማሪዎች የእግር ኳስ ______________ አቋቋሙ።
5. መሰለች ______________ ገብታ መፅሐፍ አነበበች።
6. ጎበዟ ተማሪ ዘወትር ______________ ።
7. ለእግረኛ በተፈቀደው ______________ አቋረጡ።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የምታዉቁትን ተረት በክፍል ውስጥ ተናገሩ።
2. የንግግርን መመሪያ መሠረት በማድረግ ስለትምህርት ቤታችሁ ገፅታ ንግግር አድርጉ።
3. ስለልዩ ልዩ አባባሎች በተማራችሁት መሠረት በክፍል ውስጥ ተወያዩ።
4. ጓደኞቻችሁ በክፍል ውስጥ ተረት ሲናገሩ በማዳመጥ የተረቱን መልዕክት ተናገሩ።
5. ከምታዉቁት ተረት ውስጥ ገፀ ባህሪያትን እና ተግባራቸውን ተናገሩ።
6. ከዚህ በታች ከተሰጡ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ምክንያትና ውጤቱን በመለየት አሳዩ።

ሀ. በርትታ በማጥናት አንደኛ ወጣች

ምክንያት፡-

ውጤት፡-

ለ. ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገቡ ከትምህርት ቤት ሽልማት አገኘ።

ምክንያት፡-

ውጤት፡-

ሐ. የግል ንፅህናውን ባለመጠበቁ ታመመ

ምክንያት፡-

ውጤት፡-

መ. የትምህርት ቤቱን ህግ ባለማክበሩ ተባረረ።

ምክንያት፡-

ውጤት፡-

ዋቢ ፅሁፍ

**ሳባ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።(2005ዓ.ም)። አዲስ አበባ ፣አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።**

**ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስትቲዩት ።(1995ዓ.ም)። የኤች አይቪ ኤድስ ትምህርት። አዲስ አበባ ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።**

**ታለጌታ ይመር ።(2007 ዓ.ም)። ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ። ብረሃና ማተሚያ ድርጅት።**

ከበደ ሚካኤል፡፡(1999**ዓ.ም**)፡፡ታሪክናምሳሌ፡፡አንደኛ መጽሀፍ፡፡2ኛ እትም**፣አዲስ አበባ** ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡፡

ኢትዮጲስ ቁጥር 2 የልጆች የተረት መፅሀፍ፡፡

http://am.Wikipedia.org ›wiki›

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
# የተማሪ መጽሐፍ አራተኛ ክፍል

## አራተኛ ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ